# መጀመሪያው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

## ምዕራፍ ፩

፩በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ሊሆን ከተጠራ ከጳውሎስና ከወንድማ
ችን ከሶስቴንስ፥ ፪በቆሮንቶስ ሀገር ላለች ለእግ
ዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም ለከበሩና ቅዱሳን ለተባሉ የእነርሱና የእኛ
ጌታ የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን
ስም በየስፍራው ለሚጠሩ ሁሉ፥ ፫ከአባታችን
ከእግዚአብሔር፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ
ዘንድ ሰላምና ጸጋ ለእናንተ ይሁን።

፬ስለ እናንተ በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብ
ሔር ዘንድ ለእናንተ ስለተሰጣችሁ ጸጋ ዘወ
ትር እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ፭በእነጋ
ገር ሁሉ፥ በዕውቀትም ሁሉ ከብራችሁበታ
ልና። ፮ለክርስቶስ መመስከሬ በእናንተ እንደ
ጸና መጠን። ፯ፍጹማንም እንድትሆኑ፩ የጌታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስንም መምጣት ተስፋ
አድርጋችሁ ፍጹም ጸጋን እንዳታጡ፥ ፰እር
ሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ያለ
ነውር ትገኙ ዘንድ እስከ ፍጻሜ ያጸናችኋል።
፱ከልጁ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር
አንድ ትሆኑ ዘንድ የጠራችሁ እግዚአብሔር
የታመነ ነው።

### መለያየት እንደማይገባ

፲ወንድሞቻችን! አንድ ቃል እንድትናገሩ፥
እንዳታዝኑ፥ ፍጹማንም እንድትሆኑ፥ ሁላችሁ
ንም፡- በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እማ
ልዳችኋለሁ፤ እንዳትለያዩም አንድ ልብና አንድ
አሳብ ሆናችሁ ኑሩ። ፲፩ወንድሞቻችን ሆይ!
እንደምትጣሉና እንደምትከራከሩ ከቀሎኤስ ወገ
ኖች ስለ እናንተ ነገሩኝ። ፲፪እነሆ፥ እርስ በር
ሳችሁ፥ "እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔ የአጵሎስ
ነኝ፤ እኔ የኬፋ ነኝ፤ እኔ የክርስቶስ ነኝ" የም
ትሉትን እነግራችኋለሁ። ፲፫ክርስቶስ ተከፍሎ
አልን? ወይስ በውኑ ጳውሎስ ስለ እናንተ ተሰ
ቀሎአልን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠምቃች
ኋልን? ፲፬ከቀርስጶስና ከጋይዮስ በቀር ከእናንተ
ወገን ሌላ ስላላጠመቅሁ እግዚአብሔርን አመ
ሰግነዋለሁ። ፲፭በእርሱ ስም ተጠመቅን የሚል
እንዳይኖር። ፲፮ነገር ግን የእስጢፋኖስን ቤተ
ሰብእ አጥምቄአለሁ፤ እንግዲህ ሌላም ያጠመ
ቅሁት እንዳለ አላውቅም።

### ስለ መስቀል

፲፯ክርስቶስ ወንጌልን ለመስበክ እንጂ ለማ
ጥመቅ አልላከኝምና፥ የክርስቶስን መስቀሉን
ከንቱ እንዳናደርግ ነገርን በማራቀቅ አይደለም።
፲፰የመስቀሉ ነገር በሚጠፉ ሰዎች ዘንድ ስንፍና
ነውና፥ ስምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአብሔር
ኀይል ነው። ፲፱መጽሐፍ እንዲህ ብሎአልና፥
"እኔ የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የመካ
ሪዎችንም ምክር እንቃለሁ።" ፳እንግዲህ ጥበ
በኛ ማን ነው? ጸሐፊስ ማን ነው? ይህን ዓለ
ምስ የሚመረምረው ማን ነው? እግዚአብሔር
የዚህን ዓለም ጥበብ ስንፍና አላደረገውምን?
፳፩ሰዎች በጥበባቸው በማያውቁት በእግዚአብ
ሔር ጥበብ ስንፍና በሚመስላቸው ትምህርት
ያመኑትን ሊያድናቸው እግዚአብሔር ወድዶአ
ልና። ፳፪አይሁድ ምልክትን ይጠይቃሉ፤ የጽርዕ
ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ። ፳፫እኛ ግን የተሰቀለ
ውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ
ማሰናከያ ለአሕዛብም ስንፍና ነው። ፳፬ለእኛ

---

፩ "ፍጹማንም እንድትሆኑ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፩፥፲፪ ሐ.ሥ. ፲፰፥፳፬። ፩፥፲፬ ሐ.ሥ. ፲፰፥፰፤ ፲፱፥፳፱፤ ሮም ፲፮፥፳፫። ፩፥፲፮ ፩ቆሮ. ፲፮፥፲፭።
፩፥፲፱ ኢሳ. ፳፱፥፲፬። ፩፥፳ ኢዮብ ፲፪፥፲፯፤ ኢሳ. ፲፱፥፲፪፤ ፴፫፥፲፰፤ ፵፬፥፳፭።

ለዳንነው[፪] ግን ከአይሁድ፥ ከአረማውያንም ብንሆን
ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይል ነው፤ የእግዚ
አብሔርም ጥበብ ነው። ፳፭የእግዚአብሔር ስን
ፍና ከሰው ይልቅ ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔ
ርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና።
፳፮ወንድሞቻችን! እንግዲህ እንዴት እንደ
ተጠራችሁ እዩ፤ በሥጋ እጅግ ብዙዎች ዐዋቂ
ዎች አይደላችሁምና፥ ብዙዎች ኀያላንም አይ
ደላችሁምና፥ በዘመድም ብዙዎች ደጋጎች አይ
ደላችሁምና። ፳፯ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበ
ኞችን ሊያሳፍር የዚህን ዓለም ሰነፎች መረጠ፤
ኀይለኞችንም ያሳፍር ዘንድ እግዚአብሔር የዚ
ህን ዓለም ደካሞች መረጠ። ፳፰እለን የሚሉት
ንም ያሳፍር ዘንድ ዘመድ የሌላቸውንና የተና
ቁትን፥ ከቍጥርም ያልገቡትን እግዚአብሔር
መረጠ። ፳፱ስው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እን
ዳይመካ። ፴እናንተም በኢየሱስ ክርስቶስ ከእ
ርሱ ናችሁ፤ በእርሱም ከእግዚአብሔር ጥበብ
ንና ጽድቅን፥ ቅድስናንና ቤዛነትን አገኘን።
፴፩መጽሐፍ እንደ አለው ይሆን ዘንድ "የሚመ
ካ በእግዚአብሔር ይመካ።"

## ምዕራፍ ፪

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ እኔም ወደ እናንተ
በመጣሁ ጊዜ በማባበልና ነገርን በማራቀቅ የእ
ግዚአብሔርን ትምህርት ላስተምራችሁ የመ
ጣሁ አይደለም። ፪ከተሰቀለው ከኢየሱስ ክር
ስቶስ በቀር በእናንተ ዘንድ ሌላ ነገር እስ
ማለሁ ብዬ አልጠረጠርሁም ነበር። ፫እኔም
በድካምና በፍርሀት፥ በብዙ መንቀጥቀጥም
መጣሁ።[፩] ፬ቃሌም፥ ትምህርቴም መንፈስንና
ኀይልን በመግለጥ ነበር እንጂ በሚያባብል በጥ
በብ ቃል አልነበረም። ፭ማመናችሁ በእግዚአ
ብሔር ኀይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን።

### ስለ እውነተኛ ጥበብ

፮ለዐዋቆች ጥበብን እንነግራቸዋለን፤ ነገር
ግን የዚህን ዓለም ጥበብ ወይም ያልፉ ዘንድ
ያላቸውን የዚህን ዓለም ሹሞች ጥበብ አይደ
ለም። ፯ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘ
መናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን ተሰው
ሮም የነበረውን የእግዚአብሔር ጥበብ በምሥ
ጢር እንናገራለን። ፰የዚህ ዓለም ሹሞችም አላ
ወቁትም፤ ይህንስ ቢያውቁ ኖሮ የክብር ባለ
ቤትን ባልሰቀሉትም ነበር። ፱ነገር ግን መጽ
ሐፍ፥ "ዐይን ያላየው፥ ጆሮም ያልሰማው፥
በሰውም ልቡና ያልታሰበ እግዚአብሔር ለሚ
ወዱት ያዘጋጀው ነው።" ብሎ የለምን? ፲ለእ
ኛም እግዚአብሔር በመንፈሱ ገለጠልን፤ መን
ፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምሥጢ
ሩን ያውቃልና። ፲፩በሰው ልቡና ያለውን የሚ
ያውቅ ሰው ማን ነው? በእርሱ ያለችው ነፍሱ
ናት እንጂ፤ እንዲሁም ከእግዚአብሔር መን
ፈስ በቀር የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ
የለም። ፲፪እኛ የዚህን ዓለም መንፈስ የተቀበ
ልን አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠ
ንን ጸጋ እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሚሆ
ነውን መንፈስ ተቀበልን። ፲፫ይህም ትምህርታ
ችን ከሰው የተገኘ ትምህርት አይደለም፤ የእነ
ጋገር ጥበብም አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ የገ
ለጸው ትምህርት ነው እንጂ፤ መንፈሳዊ ጥበ
ብም ከመንፈስ ቅዱስ የሚሆነውን መርምረው
ለሚያውቁ ለመንፈሳውያን ነው።
፲፬ለሥጋዊ ሰው ግን የእግዚአብሔር መንፈስ
ነገር ሞኝነት ይመስለዋልና፥ አይቀበለውም፤
በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቅ አይ
ችልም። ፲፭መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን
ሁሉን ይመረምራል፤ እርሱን ግን የሚመረም
ረው የለም። ፲፮የእግዚአብሔርን አሳብ ማን
ያውቃል? መካሩስ ማን ነው? እኛ ግን ክርስ
ቶስ የሚገልጠው ዕውቀት አለን።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ መጀመሪያ ትምህርት

፩ወድሞቼ ሆይ፥ እኔስ የሥጋና የደም እንደ
መሆናችሁ፥ ክርስቶስንም በማመን ሕፃናት
እንደ መሆናችሁ እንጂ እንደ መንፈሳውያን
ላስተምራችሁ አልቻልሁም። ፪ወተትን ጋትኋ
ችሁ፤ ጽኑ መብልም ያበላኋችሁ አይደለም፤
ገና አልጠነከራችሁምና፤ ፫በሥጋዊ ሕግም ትኖ
ራላችሁና እርስ በርሳችሁ የምትቃኑና የምትከ
ራከሩ ከሆነ ግን ሥጋውያን መሆናችሁ አይደ
ለምን? እንደ ሰው ልማድስ የምትኖሩ መሆና
ችሁ አይደለምን? ፬ከመካከላችሁ፥ "እኔ የጳ
ውሎስ ነኝ" የሚል አለና፤ ሌላውም፥ "እኔ

፪ ግሪኩ "ለተጠሩት ግን ..." ይላል።

፩ ግሪኩ "በእናንተ ዘንድ ነበርሁ" ይላል።

፩፥፴፩ ኤር ፱፥፳፬። ፪፥፱ ኢሳ. ፷፬፥፬። ፪፥፲፮ ኢሳ. ፵፥፲፫። ፫፥፪ ዕብ. ፭፥፲፪-፲፫። ፫፥፬ ፩ቆሮ. ፩፥፲፪።

የአጵሎስ ነኝ” ቢል እናንተ ሥጋውያን መሆና
ችሁ አይደለምን? ፭እንግዲህ ጳውሎስ ምንድን
ነው? አጵሎስስ ምንድን ነው? እነርሱስ በቃላ
ቸው የአመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳ
ንዱም እግዚአብሔር እንደ ሰጠው ነው። ፮እኔ
ተከልሁ፤ አጵሎስም አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአ
ብሔር አሳደገ። ፯አሁንም የሚተክልም ቢሆን፥
የሚያጠጣም ቢሆን የሚጠቅመው ነገር የለም፤
የሚያሳድግ እግዚአብሔር ነው እንጂ። ፰የሚ
ተክልም፥ የሚያጠጣም አንድ ናቸው፤ ሁሉም
እንደ ድካማቸው ዋጋቸውን ይቀበላሉ። ፱በእ
ግዚአብሔር ሥራ እንተባበራለንና፤ የእግዚአብ
ሔርም አገልጋዮች፩ ነንና፤ እናንተም የእግዚአ
ብሔር ሕንጻ ናችሁ።

፲እግዚአብሔር እንደ ሰጠኝ ጸጋ መጠን
እንደ ብልህ የጠራቢዎች አለቃ ሆኜ እኔ መሠ
ረት ጣልሁ፤ ሌላውም በእርሱ ላይ ያንጻል፤
እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንደ
ሚያንጽ ይጠንቀቅ። ፲፩ነገር ግን ከተመሠረ
ተው በቀር ሌላ መሠረት ሊመሠርት የሚችል
የለም፤ መሠረቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
፲፪በዚህ መሠረት ላይ በወርቅና በብር፥ በከ
በረ ድንጋይና በእንጨት፥ በሣርና በእንጨት የሚ
ያንጽ ቢኖርም፥ ፲፫የእያንዳንዱ ሥራ ይገለ
ጣል፤ እሳትም በፈተነው ጊዜ ቀኑ ይገልጠ
ዋል፤ የእያንዳንዱንም ሥራ እሳት ይፈትነ
ዋል። ፲፬ሥራው ጸንቶ የተገኘለት ሰው ዋጋ
ውን የሚቀበል እርሱ ነው። ፲፭ሥራው የተቃ
ጠለበት ግን ዋጋውን ያጣል፤ እርሱም ከእ
ሳት እንደሚድን ሰው ይድናል።

፲፮እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ
ሆናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንፈስም በእናንተ
ላይ አድሮ እንደሚኖር አታውቁምን? ፲፯የእግ
ዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የሚያፈርሰውን ግን
እርሱን ደግሞ እግዚአብሔር ያፈርሰዋል፤ የእ
ግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነውና፤ የእግዚአብ
ሔር ቤተ መቅደስም እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፤
እንግዲያስ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አታ
ርክሱ።፪

፲፰ራሳችሁን አታስቱ፤ ከመካከላችሁ በዚህ
ዓለም ጥበበኛ እንደ ሆነ የሚያስብ ሰው ጥበበኛ
ይሆን ዘንድ ራሱን ዕላዋቂ ያድርግ። ፲፱የዚህ
ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ዘንድ ድንቍርና
ነውና፤ መጽሐፍ እንዲህ ብሎአልና፥ “ጠቢባ
ንን የሚገታቸው ተንኰላቸው ነው።” ፳ዳግ
መኛ “የጥበበኞች አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ እግዚ
አብሔር ያውቃል” ብሎአል። ፳፩ስለዚህም እን
ግዲህ አንዱ ስንኳ በሰው አይመካ፤ ሁሉ የእ
ናንተ ነውና። ፳፪ጳውሎስም ቢሆን፥ አጵሎስም
ቢሆን፥ ጴጥሮስም ቢሆን፥ ዓለምም ቢሆን፥
ሕይወትም ቢሆን፥ ሞትም ቢሆን፥ ያለውም
ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን ሁሉ የእናንተ
ነው። ፳፫እናንተ ግን የክርስቶስ ናችሁ፤ ክርስ
ቶስም የእግዚአብሔር ነው።

## ምዕራፍ ፬

## ስለ ሐዋርያዊ አገልግሎት

፩እኛ የክርስቶስ አገልጋዮችና የእግዚአብሔር
የምሥጢሩ መጋቢዎች እንደ ሆን ሰው ስለ እኛ
እንዲህ ያስብ። ፪እንግዲህ በዚህ ከመጋቢዎች
እያንዳንዱ ቸርና ታማኝ ሆኖ እንዲገኝ ይፈለ
ጋል። ፫ለእኔስ በእናንተ ዘንድ መመስገን ውር
ደት ነው፤ ጻድቅ ብትሉኝ፥ በመዋቲ ሰው ዘን
ድም ቸር ብላችሁ ብታከብሩኝ እኔ ስራሴ
እልፈርድም።፩ ፬የሚያጠራጥረኝና ትዝ የሚለኝ
ነገር የለም፤ በዚህም ራሴን አላመጻድቅም፤
እግዚአብሔር ይመረምረኛልና። ፭ጊዜው ሳይ
ደርስ ዛሬ ለምን ትመረምራላችሁ? በጨለማ
ውስጥ የተሰወረውንም የሚያበራ፥ የልብን አሳ
ብም የሚገልጥ ጌታችን ይመጣል፤ ያንጊዜ
ሁሉም ዋጋውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀ
በላል።

፮ወንድሞቻችን ሆይ! እኔም፥ አጵሎስም ብን
ሆን መከራ የተቀበልነው ስለ እናንተ ነው፤ እና
ንተ እንድትማሩ፥ ከመጻሕፍት ቃልም ወጥታ
ችሁ በወንድሞቻችሁ ላይ እንዳትታበዩ ነው።
፯ማን ይመረምርሃል?፪ የምትታበይስ በምንድን

---

፩ በግሪኩ “የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ” ይላል።

፪ “እንግዲያስ የአግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አታርክሱ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፩ ምዕ. ፬ ቁ. ፫ በግሪኩ “ነገር ግን በእናንተ ዘንድ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ቢፈረድብኝ ለእኔ ምንም አይደለም እኔም በራሴ እንኳ አልፈርድም” ይላል።

፪ ግሪኩ “አንተን ከሌላው ልዩ ያደረገህ ማን ነው” ይላል።

፫፥፮ ሐ.ሥ. ፲፰፥፩-፲፩፤ ፳፬፥፳፰። ፫፥፲፮ ፩ቆሮ. ፮፥፲፱፤ ፪ቆሮ. ፮፥፲፮። ፫፥፲፱ ኢዮብ ፭፥፲፫።
፫፥፳ መዝ. ፺፫፥፲፩።

ነው? ከሌላ ያላገኘኸው አለህን? ያለህንም
ከሌላ ካገኘህ እንዳላገኘ ለምን ትኮራለህ?
፰እናንተ አሁን ጠግባችኋል፤ በልጽጋች
ኋልም፤ ያለእኛም ፈጽማችሁ ነግሣችኋል፤
እኛም ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ
አግባብ በሆነ ነበር። ፱እኔስ ለሞት ዝግጁዎች
እንደ መሆናችን እኛን ሐዋርያቱን እግዚአብ
ሔር የኋለኞች ያደረገን ይመስለኛል፤ እኛ ለሰ
ዎችም፥ ለመላእክትም፥ ለዓለምም መዘባበቻ
ሆነናልና። ፲እኛስ ስለ ክርስቶስ ብለን አላዋ
ቂዎች ነን፤ እናንተ ግን በክርስቶስ ጠቢባን
ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን፤ እናንተ ግን ብርቱ
ዎች ናችሁ፤ እናንተ ክቡራን ናችሁ፤ እኛ ግን
የተዋረድን ነን። ፲፩እኛ እስከዚች ቀን ድረስ
እንራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቈታለን፤ እንሰ
ደዳለን፤ ማረፊያም የለንም፤ እንደበደባለንም።
፲፪በእጃችን ሥራ እያገለገልን እንደክማለን፤ ይረ
ግሙናል፤ እኛ ግን እንመርቃቸዋለን፤ ያሳድ
ዱናል፤ እኛ ግን እንጸልይላቸዋለን፤ እንታገሣ
ቸዋለንም። ፲፫ይሰድቡናል፥ እንማልዳቸዋለን፤
በዓለም እንደ ጉድፍ ሆንን፤ በሁሉም ዘንድ የተ
ናቅን ሆንን።
፲፬ይህንም የጻፍሁላችሁ ላሳፍራችሁ አይደ
ለም፤ ልጆቼና ወዳጆቼ እንደ መሆናችሁ ልመ
ክራችሁና ላስተምራችሁ ነው እንጂ፤ እኔ ለሁ
ላችሁ ቤዛችሁ ነኝ፤ እናንተ ግን አላፈራችሁ
ኝም።፫ ፲፭በክርስቶስ ብዙ መምህራን ቢኖሩእ
ችሁም አባቶቻችሁ ብዙዎች አይደሉም፤ እኔ
በኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርት ወልጄአችኋለ
ሁና።

### መምህራንን ስለ መምሰል

፲፮ወንድሞቻችን ሆይ! እኔን እንድትመስሉ
እማልዳችኋለሁ፤ ፲፯ስለዚህም በየስፍራው በአ
ብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዳስተማርሁ በክ
ርስቶስ ኢየሱስ የሄድሁበትን መንገድ ይገል
ጥላችሁ ዘንድ በእግዚአብሔር የታመነና ልጄ
ወዳጄ የሆነ ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ።
፲፰እነሆ፥ ወደ እናንተ ስላልመጣሁ ከእናንተ
ወገን የታበዩ ሰዎች አሉ። ፲፱እንኪያስ እግዚአብ
ሔር ቢፈቅድ ፈጥኜ እመጣለሁ፤ ነገር ግን የት
ዕቢተኞችን ነገር አልሻም፤ ኀይላቸውን እሻለሁ
እንጂ። ፳የእግዚአብሔር መንግሥት በኀይል
እንጂ በቃል አይደለምና። ፳፩እንዴት ሆኜ ወደ
እናንተ ልመጣ ትወዳላችሁ? በበትር ነውን?
ወይስ በፍቅርና በቅንነት መንፈስ?

## ምዕራፍ ፭

### የማይገባ ሥራ በሚሠሩ ላይ የሚሰጥ ቅጣት

፩በእናንተ ላይ ዝሙት ይሰማል፤ እንደዚህ
ያለው ዝሙትም አረማውያን እንኳ የማያደር
ጉት ነው፤ ያባቱን ሚስት ያገባ አለና። ፪እናን
ተም ከዚህ ጋር ትዕቢተኞች ናችሁ፤ ይልቁንም
ይህን ያደረገው ከእናንተ ይለይ ዘንድ ለምን
አላዘናችሁበትም? ፫እኔ በሥጋዬ ከእናንተ
ጋር ባልኖር፥ በመንፈሴ ከእናንተ ጋር አለሁ፤
እነሆ፥ ከእናንተ ጋር እንደ አለሁ ሆኜ፥ ይህን
ሥራ የሠራውን አፈርድበታለሁ። ፬በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስባችሁ፥ በእኔ
ሥልጣን፥ በጌታችን በኢየሱስም ኀይል፥ ፭ሥጋ
ውን ጎድቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመ
ጣበት ቀን ነፍሱ ትድን ዘንድ እንዲህ ያለውን
ሰው ለሰይጣን አሳልፋችሁ ስጡት።
፮እንግዲያስ መታበያችሁ መልካም አይደ
ለም፤ ጥቂቱ እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያ
መጥ አታውቁምን? ፯እንግዲህ ለአዲስ ቡሆ
ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ ከእናንተ አርቁ፤
ገና ቂጣ ናችሁና፤ ፋሲካችን ክርስቶስ ተሠ
ውቶ የለምን? ፰አሁንም በዓላችሁን አድርጉ፤
ነገር ግን እውነትና ንጽሕና ባለው እርሾ ነው
እንጂ በአሮጌው እርሾ፥ በኀጢአትና በክፋት
እርሾም አይደለም።
፱ከዘማውያን ጋር አንድ እንዳትሆኑ በዚህ
መልእክት ጻፍሁላችሁ። ፲የዚህ ዓለም ዝሙት
ብቻ አይደለም፤ ቀማኞችና ዘራፊዎች፥ ጣዖ
ትን የሚያመልኩ ደግሞ አሉ፤ ያለዚያስ ከዚህ
ዓለም ልትለዩ ይገባል።፬ ፲፩አሁንም ከወንድ
ሞች መካከል ዘማዊ፥ ወይም ገንዘብን የሚ
መኝ፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ፥ ወይም
ዐመፀኛ፥ ወይም ተራጋሚ፥ ወይም ሰካራም፥
ወይም የሚቀማ ቢኖር እንደዚህ ካለ ሰው ጋር

---

፫ “እኔ ለሁላችሁ ቤዛችሁ ነኝ እናንተ ግን አላፈራችሁኝም” የሚለው በግሪኩ የለም።
፬ ምዕ. ፭ ቍ. ፲ ግሪኩ “በጠቅላላው የዚህ ዓለም ሴሰኞችን ወይም ገንዘብ የሚመኙትን ነጣቂዎችንም ወይም ጣዖ
ትን የሚያመልኩትን አላልሁም ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር” ይላል።
፬፥፲፪ ሐ.ሥ. ፲፰፥፫። ፬፥፲፯ ፩ቆሮ. ፲፩፥፩፤ ፊል. ፫፥፲፯። ፭፥፩ ዘሌ. ፲፰፥፰። ፭፥፯ ገላ. ፭፥፱።
፭፥፯ ዘፀ. ፲፪፥፭። ፭፥፰ ዘፀ. ፲፫፥፫፤ ዘዳ ፲፯፥፫።

አንድ እንዳትሆኑ ጻፍሁላችሁ፥ እንደዚህ ካለው
ሰው ጋር መብልም እንኳ አትብሉ፤[፱] ፲፪ምን
አግዶኝ፥ በውጭ ባለው ላይ እፈርድበታለሁ?
እናንተስ በውስጥ ከእናንተ ጋር የሚኖሩትን
ፈርዳችሁ ቅጡአቸው።[፲] ፲፫በውጭ ያሉትን
ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል፤ ይቀጣቸዋ
ልም፤ ክፉውን ከእናንተ አርቁ።

## ምዕራፍ ፮

### በዐመፀኞች ዳኝነት መከራከር ስለማይገባ

፩እንግዲህ በሚነቅፉ ሰዎች ዘንድ ልትከራከሩ
አትድፈሩ፤ ከጓደኛው ጋር በዐመፀኞች ዘንድ
ሊከራከር የሚችል አለን? በደጋጎች ዘንድ አይ
ደለምን? ከባልንጀራው ጋር ክርክር ያለው ቢኖ
ርም በቅዱሳን ዘንድ ይከራከር፤ በሚነቅፉና
በዐመፀኞች ዘንድ ግን አይደለም።[፩] ፪ቅዱሳን
ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ አታውቁምን? እና
ንተ ሰውን ሁሉ የምትዳኙ ከሆናችሁ ይህን
ትንሹን ነገር ልትዳኙ አይገባችሁምን? ፫የዚህ
ንስ ዓለም ዳኝነት ተዉትና በመላእክት ስንኳ
እንድንፈርድ አታውቁምን? ፬ነገር ግን የዚህ
ዓለም ክርክር ያላቸው ሰዎች ቢኖሩ በቤተ ክር
ስቲያን የተሾሙ የበታች ወንድሞች ይስሙአ
ቸው። ፭ይህንም የምላችሁ ስለፋችሁ ነው፤
እንግዲህ ከመካከላችሁ ወንድማማቾችን ከወን
ድሞቻቸው ጋር ማስታረቅ የሚችል ሽማግሌ
የለምን? ፮ነገር ግን ወንድም ከወንድሙ ጋር
ይካሰሳል፤ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋል።
፯እንግዲህ ጸብና ክርክር ካላችሁ፥ ከመጀመሪ
ያው ጀምሮ ውርደት እንደሚሆንባችሁ ዕወቁ፤
እንግዲያማ እንዴት አትነጠቁም? እንዴትስ
አትገፉም? ፰አሁንም ቢሆን፥ እናንተ ዐመፀኞ
ችና ቀማኞች ናችሁ፤ እንደዚህም ወንድሞቻ
ችሁን ትበድላላችሁ።

### መንግሥተ ሰማያትን ስለማይወርሱ ሰዎች

፱ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እን
ደማይወርሱ አታውቁምን? አያስቱአችሁ፤ ሴሰ
ኞች፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ፥ ወይም
አመንዝራዎች፥ ወይም ቀላጮች፥ ወይም በወ
ንድ ላይ ዝሙትን የሚሠሩ፥ የሚሠሩባቸውም
ቢሆኑ፤ ፲ሌቦች፥ ወይም ቀማኞች፥ ወይም
ሰካሮች፥ ወይም ተሳዳቢዎች፥ ወይም ነጣቂ
ዎች፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱ
አትም። ፲፩እንግዲህ እናንተ እንዲህ ስትሆኑ እነ
ማን ናችሁ? ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክር
ስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባች
ኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋልም።

### ሰውነትን ለእግዚአብሔር ክብር ስለ ማድረግ

፲፪በሆነው ሁሉ ላይ ሥልጣን አለኝ፤ ግን ሁሉ
የሚጠቅመኝ አይደለም፤ ሁሉም ይቻለኛል፤
ነገር ግን በእኔ ላይ እንዲሠለጥን የማደርገው
ምንም የለም። ፲፫መብል ለሆድ ነው፤ ሆድም
ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም
ይሽራቸዋል፤ ሥጋችሁም ለእግዚአብሔር ነው
እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ እግዚአብሔርም
ለሥጋችሁ ነው። ፲፬ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን
ከሙታን ያስነሣው እግዚአብሔር እኛንም በከሃ
ሊነቱ ያስነሣናል። ፲፭ሥጋችሁ የክርስቶስ አካል
እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን
አካል ወስዳችሁ የአመንዝራ አካል ታደርጉታ
ላችሁን? አይገባም። ፲፮ከአመንዝራ ጋር የተገ
ናኘ ከእርስዋ ጋር አንድ አካል እንዲሆን አታ
ውቁምን? መጽሐፍ፥ "ሁለቱ አንድ አካል ይሆ
ናሉ" ብሎአልና። ፲፯ከእግዚአብሔር ጋር የተዋ
ሐደ ግን ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ይሆናል።
፲፰ከዝሙት ራቁ፤ ኀጢአት የሚሠራ ሰው ሁሉ
ከሥጋው ውጭ ይሠራልና፤ ዝሙትን የሚሠራ
ግን ራሱ በሥጋው ላይ ኀጢአትን ይሠራል።
፲፱ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር ለተቀበላችሁት በእ
ናንተ አድሮ ላለ ለመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ
እንደ ሆነ አታውቁምን? ለራሳችሁም አይደላች
ሁም። ፳በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህም እግ
ዚአብሔርን በሥጋችሁ አክብሩት።

## ምዕራፍ ፯

### ስለ ጋብቻ

፩ስለ ጻፋችሁልኝስ ለሰው ወደ ሴት አለመ
ቅረብ ይሻለዋል። ፪ነገር ግን እንዳትሴስኑ ሰው

---

፱ "እንደዚህ ካለው ሰው ጋር መብልም እንኳ አትብሉ" የሚለውን ግእዙ አይጽፍም።

፲ "ቅጡአቸው" የሚለው በግሪኩ የለም።

፩ ምዕ. ፮ ቍ. ፩ ግእዙ "እንግዲህ በሚነቅፉ ሰዎች ልትከራከሩ አትድፈሩ፤ ከጓደኛው ጋር በዐመፀኞች ዘንድ ሊከራ ክር የሚችል አለን? በደጋጎች ዘንድ አይደለምን" የሚል ዘር በመጨመር ከግሪኩ ይለያል።

፮፥፩ ፩ ቆሮ. ፲፥፳፫። ፮፥፲፮ ዘፍ. ፪፥፳፬። ፮፥፲፱ ፩ ቆሮ. ፫፥፲፮፤ ፪ቆሮ. ፮፥፲፮።

ሁሉ በሚስቱ ይወሰን፤ ሴትም ሁላ በባልዋ
ትወሰን። ፫ለሚስትም ባልዋ የሚገባትን ያድር
ግላት፤ እንዲሁ ሚስትም ለባልዋ የሚገባውን
ታድርግለት። ፬ሚስት በራስዋ አካል ሥልጣን
የላትም፤ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲ
ሁም ባል በራሱ አካል ሥልጣን የለውም፤
ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ፭ለጸሎት እን
ድትተጉ ከምትስማሙበት ጊዜ ብቻ በቀር፥
ባልና ሚስት አትለያዩ፤ ዳግመኛ ሰይጣን ድል
እንዳያደርጋችሁ በአንድነት ኑሩ፤ ሰውነታ
ችሁ ደካማ ነውና ። ፮ይህንም የምላችሁ እንደ
ፈቃድ ነው እንጂ፥ ላዝዛችሁ አይደለም። ፯ሰው
ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን
ሰው ሁሉ እግዚአብሔር እንደ አደለው ጸጋ
ይኑር፤ ግብሩ እንዲህ የሆነ አለና፤ ግብሩ ሌላ
የሆነም አለና።

፰ነገር ግን ያላገቡትንና አግብተው የፈቱትን
እንደ እኔ ሆነው ቢኖሩ ይሻላቸዋል እላለሁ።
፱መታገሥ ባይችሉ ግን ያግቡ፤ በፍትወት ከመ
ቃጠል ማግባት ይሻላልና። ፲ያገቡትንም በእግ
ዚአብሔር ትእዛዝ አዝዛቸዋለሁ፤ በራሴ ትእዛ
ዝም አይደለም፤ ሚስትም ከባልዋ አትፋታ።
፲፩ከተፋታችም ብቻዋን ትኑር፤ ያለዚያ ከባልዋ
ጋር ትታረቅ፤ ባልም ሚስቱን አይፍታ።

፲፪ሌላውን ግን ከራሴ እናገራለሁ፤ ከጌታ
ችንም አይደለም፤ ከወንድሞቻችን መካከል
የማታምን፥ ባልዋንም የምታፈቅር[፩] ከእርሱም
ጋር ለመኖር የምትወድ ሚስት ያለችው ሰው
ቢኖር ሚስቱን አይፍታ። ፲፫ሴቲቱም የማያም
ንና ሚስቱንም የሚያፈቅር[፪] ከእርስዋም ጋር
ሊኖር የሚወድ ባል ቢኖራት ባልዋን አትፍታ።
፲፬የማያምን ባል በሚስቱ ይቀደሳልና፤ የማታ
ምን ሚስትም በባልዋ ትቀደሳለችና፤ ያለዚያማ
ልጆቻቸው ርኩሳን ይሆናሉ፤ አሁን ግን ቅዱ
ሳን ናቸው። ፲፭የማያምን ግን ቢፈታ ይፍታ፤
ወንድምና እኅት እግዚአብሔር ለሰላም ስለ
ጠራቸው እንደዚህ ላለ ግብር አይገዙምና።
፲፮ሚስትም ባልዋን ታድነው እንደ ሆነ አታ
ውቅምና፤ ባልም ሚስቱን ያድናት እንደ ሆነ
አያውቅምና።

፲፯ነገር ግን ሁሉ እግዚአብሔር እንደ አደ
ለው፥ ሁሉም እግዚአብሔር እንደ ጠራው እን
ዲሁ ይኑር፤ ለአብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ
እንዲህ ሥርዐት እንሠራለን። ፲፰ተገዝሮ ሳለ
የተጠራ ቢኖር አለመገዘርን አይመኝ፤ ያልተገዘ
ረም ቢጠራ ከዚያ ወዲያ አይገዘር። ፲፱የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ መገዘርም
አይጠቅምም፤ አለመገዘርም አይጎዳም።

## ወደ ሃይማኖት ስለ መጠራት

፳ሁሉ እንደ ተጠራ እንዲሁ ይኑር። ፳፩አንተ
ባርያ ሳለህ ብታምን አያሳዝንህ፤ የሚቻልህ
ከሆነ ግን ነጻነትህን አግኝ። ፳፪የተጠራ ባሪያ
በእግዚአብሔር ዘንድ ነጻነት ያለው ነውና፤ እን
ዲሁ ነጻነት ያለውም ከተጠራ የክርስቶስ ባርያ
ነው። ፳፫በዋጋ ገዝቶአችኋልና የሰው ተገዦች
አትሁኑ። ፳፬ወንድሞቻችን ሁላችሁም በተጠራ
ችሁበት እንዲሁ በእግዚአብሔር ኑሩ።

## ስለ ደናግልና ስለ መዓስባት

፳፭ስለ ደናግልም የምነግራችሁ የእግዚአብ
ሔር ትእዛዝ አይደለም፤ ታማኝ እንድሆን እግ
ዚአብሔር ይቅር ያለኝ እንደ መሆኔ ምክሬን
እነግራችኋለሁ እንጂ። ፳፮ነገር ግን እንዲህ ይመ
ስለኛል፤ በግድ ይህ ሊመረጥ ይሻላልና እንዲህ
ሆኖ ቢኖር ለሰው ይሻለዋል። ፳፯ከሚስትህ ጋር
ሳለህ ከእርስዋ መፋታትን አትሻ፤ ሚስት ከሌ
ለህ ግን ሚስትን አትሻ። ፳፰ብታገባም ኀጢአት
አይሆንብህም፤ ድንግሊቱም ባል ብታገባ ኀጢ
አት አይሆንባትም፤ ያገቡ ግን ለራሳቸው ድካ
ምን ይሻሉ፤ እኔም ይህን የምላችሁ ስለማዝን
ላችሁ ነው። ፳፱ነገር ግን ወንድሞቻችን እንዲህ
ይቀናል፤ የዚህ ዓለም ኑሮ ሁሉ ሊያልፍ ቀር
ቦአልና፤ አሁንም ያገቡ እንዳላገቡ ይሆናሉ።
፴ያለቀሱ እንዳላለቀሱ ይሆናሉ፤ ደስ ያላቸውም
ደስ እንዳላላቸው ይሆናሉ፤ የሸጡም እንዳል
ሸጡ ይሆናሉ፤ የገዙም እንዳልገዙ ይሆናሉ።
፴፩የበሉ እንዳልበሉ ይሆናሉ፤ የጠጡም እንዳ
ልጠጡ ይሆናሉ፤ የዚህ ዓለም ተድላ ሁሉ
ያልፋልና።

፴፪እኔስ ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ፤ ያላገባ
እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኘው የእግዚአብሔርን
ነገር ያስባልና። ፴፫ያገባ ግን ሚስቱን ደስ ሊያ
ሰኝ የዚህን ዓለም ኑሮ ያስባል። ፴፬እንዲህ ከሆነ
ግን ተለያየ፤ አግብታ የፈታች ሴትም ያላገባች
ድንግልም ብትሆን ነፍስዋም ሥጋዋም ይቀደስ

---

፩ "ባልዋን የምታፈቅር" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ "ሚስቱን የሚያፈቅር" የሚለው በግሪኩ የለም።

፯፥፲-፲፩ ማቴ. ፭፥፴፪፤ ፲፱፥፱፤ ማር. ፲፥፲፩-፲፪፤ ሉቃ. ፲፮፥፲፰።

ዘንድ እግዚአብሔርን ታስበዋለች፤ ያገባች ግን
ባልዋን ደስ ልታሰኝ የዚህን ዓለም ኑሮ ታስ
ባለች። ፴፭ ይህንም የምላችሁ እንዲጠቅማችሁ
ነው፤ ላጠምዳችሁ ግን አይደለም፤ ኑሮአችሁ
አንድ ወገን እንዲሆንና እግዚአብሔርን ያለመ
ጠራጠር እንድታገለግሉት ነው እንጂ።
፴፮ በሽመገለ ጊዜ ስለ ድንግልናው እንደሚያ
ፍር የሚያስብ ሰው ቢኖር እንዲህ ሊሆን ይገ
ባል፤ የወደደውን ያድርግ፤ ቢያገባም ኀጢአት
የለበትም። ፴፯ በልቡ የቈረጠና ያላወላወለ ግን
የወደደውን ሊያደርግ ይችላል፤ ግድም አይበ
ሉት፤ ድንግልናውንም ይጠብቅ ዘንድ በልቡ
ቢጸና መልካም አደረገ። ፴፰ ድንግሊቱን ያገባ
መልካም አደረገ፤ ያላገባ ግን የምትሻለውን
አደረገ።
፴፱ ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሠረች ናት፤
ባልዋ የሞተ እንደ ሆነ ግን ነጻ ናት፤ የወደደች
ውን ታግባ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ይሁን።
፵ በምክሬ ጸንታ እንዲሁ ብትኖር ግን ብፅዕት
ናት፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእኔ ላይ ያለ
ይመስለኛል።

## ምዕራፍ ፰

### ለጣዖት የተሠዋውን መብላት ስለማይገባ

፩ ለጣዖታት ስለሚሠዉ መሥዋዕቶች ሁላች
ንም ዕውቀት እንዳለን እናውቃለን፤ ዕውቀት
ያስታብያል፤ ፍቅር ግን ያንጻል። ፪ ዐወቅሁ
የሚል ቢኖር፥ ሊያውቅ የሚገባውን ገና አላ
ወቀም። ፫ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ግን
እርሱ በእርሱ ዘንድ በእውነት የታወቀ ነው።
፬ ለጣዖታት የተሠዋውን ስለመብላት ግን
ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ፥ ከአንድ
እግዚአብሔርም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ
እናውቃለን። ፭ አማልክት የሚሉአቸው ነገሮች
አሉና፤ በሰማይም ቢሆን፥ በምድርም ቢሆን፥
ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች ቢኖሩ፥ ፮ ለእኛስ
ሁሉ ከእርሱ የሆነ፥ እኛም ለእርሱ የሆን አንድ
እግዚአብሔር አብ አለን፤ ሁሉ በእርሱ የሆነ፥
እኛም በእርሱ የሆን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክር
ስቶስም አለን። ፯ ነገር ግን ሁሉ የሚያውቀው
አይደለም፤ እስከ ዛሬ በጣዖታት ልማድ፥ ለጣ
ዖት የተሠዋውን የሚበሉ አሉ፤ ኅሊናቸውም
ደካማ ስለሆነ ይረከሳል። ፰ መብል ግን ወደ
እግዚአብሔር አያደርሰንም፤ ብንበላም አይረባ
ንም፤ ባንበላም አይጎዳንም። ፱ ነገር ግን እናን
ተን በማየት ሌላው እንዳይሰናከል[፩] ተጠንቀቁ።
፲ አንተ እማኙ[፪] በጣዖት ቤት በማዕድ ተቀም
ጠህ ያየህ ቢኖር ያ ልቡ ደካማ የሆነ ሰው
ወዲያው ለጣዖት የተሠዋውን ደፍሮ ይበላል።
፲፩ ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተለት ያ ደካማ ወን
ድም አንተን በማየት[፫] ይጎዳል። ፲፪ በባልንጀሮ
ቻችሁ ላይ እንዲህ የምትበድሉ ከሆነ ደካማ
ሕሊናቸውንም የምታቈስሉ ከሆነ ክርስቶስን
ትበድላላችሁ። ፲፫ ነገር ግን በመብል ምክንያት
ወንድሜ የሚሰናከል ከሆነ ወንድሜን እንዳላሰ
ናክል ለዘለዓለም ሥጋን አልበላም።

## ምዕራፍ ፱

### ስለ ራሱና ስለ በርናባስ

፩ እኔ ነጻ አይደለሁምን? ሐዋርያስ አይደለሁ
ምን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያየሁ አይደ
ለሁምን? እናንተስ በጌታችን ሥራዬ አይደላች
ሁምን? ፪ ለሌሎች ሐዋርያቸው ባልሆንም ለእ
ናንተስ ሐዋርያችሁ እኔ ነኝ፤ በጌታችን የሐ
ዋርያነቴ ማኅተም እናንተ ናችሁና። ፫ ለሚከራ
ከሩኝ መልሴ እንዲህ ነው። ፬ በውኑ ልንበላና
ልንጠጣ አይገባንምን? ፭ እንደ ሌሎች ሐዋር
ያት ሁሉና፥ እንደ ጌታችን ወንድሞች እንደ
ኬፋም ከሴቶች እኅታችንን ይዘን ልንዞር አይገ
ባንምን? ፮ ወይስ ሥራን ለመተው መብት የሌ
ለን እኔና በርናባስ ብቻ ነን? ፯ የሚያገለግልም
ምግቡን ያገኝ ዘንድ ነው፤[፬] ወይን ተክሎ ፍሬ
ውን የማይበላ ማን ነው? መንጋውንስ ጠብቆ
ወተቱን የማይጠጣ ማን ነው?
፰ በውኑ ለሰው ይምሰል እናገራለሁን? የሙሴ
መጽሐፍ ኦሪትስ እንዲህ ብሎ የለምን፦ ፱ "አህ
ልህን በምታበራይበት ጊዜ የበሬውን አፉን አት
ስረው።" እንግዲህ ይህን የጻፈ ለእግዚአብሔር

---

፩ ግሪኩ "ይህ መብላታችሁ ለደካሞች እንቅፋት እንዳይሆን ..." ይላል።

፪ ግሪኩ "ዕውቀት ያለህ" ይላል።

፫ ግሪኩ "በአንተ ዕውቀት" ይላል።

፬ ግሪኩ "ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው" ይላል።

፰፥፩ ሐ.ሥ. ፲፭፥፳፱። ፰፥፬ ዘዳ. ፬፥፴፱። ፰፥፮ ሚል. ፪፥፲። ፰፥፲፫ ሮም. ፲፬፥፳፩።

፱፥፱ ዘዳ. ፳፭፥፬፤ ፩ ጢሞ. ፭፥፲፰።

በሬ አሳዝኖት ነውን? ፲ይህን የሚለው ፈጽሞ
ስለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ ሊያ
ርስ፥ የሚያበራይም እንዲካፈል በተስፋ ሊያ
በራይ ስለሚገባው በእውነት ስለ እኛ ተጽፎ
አል። ፲፩እኛ መንፈሳዊውን ነገር ከዘራንላችሁ
ሥጋዊውን ነገር ብናጭድ ታላቅ ነገር ነውን?
፲፪በእኛ ሹመት ሌላ የሚቀድመን ከሆነ የሚሻ
ላችሁን እናንተ ታውቃላችሁ፤ እኔ ይህን አል
ፈለግሁትም፤[፱] ነገር ግን የክርስቶስን ትምህ
ርት እንዳላሰናክል በሁሉ እታገሣለሁ። ፲፫የጣዖ
ታቱ ካህናት የጣዖታቱን መባ እንደሚበሉ አታ
ውቁምን? መሠዊያውን የሚያገለግሉም መሥ
ዋዕቱን እንደሚካፈሉ አታውቁምን? ለቤተ
እግዚአብሔር ሹሞች መተዳደሪያቸው የቤተ
እግዚአብሔር መባ ነው።[፲] ፲፬ጌታችንም እን
ዲሁ ወንጌልን ለሚያስተምሩ ሰዎች ለሕይወ
ታቸው መተዳደሪያ በዚያው ወንጌልን በማስ
ተማር ይሆን ዘንድ አዘዘ። ፲፭እኔ ግን ይህንም
ቢሆን አልፈቀድሁትም፤ ይህን የጻፍሁም ይህን
እንዳገኝ ብዬ አይደለም፤ እኔ ግን ምስጋናዬ
ከሚቀርብኝ ሞት ይሻለኛል። ፲፮ወንጌልን ባስ
ተምርም መመስገን አይገባኝም፤ ታዝዤ አድ
ርጌዋለሁና፤ ወንጌልን ባላስተምር ደግሞ ወዮ
ልኝ። ፲፯ይህንስ በፈቃዴ አድርጌው ብሆን ዋጋ
ዬን ባገኘሁ ነበር፤ በግድ ከሆነ ግን በተሰጠኝ
መጋቢነት አገለግልሁ። ፲፰እንግዲህ ዋጋዬ ምን
ድን ነው? ወንጌልን ባስተምርም በሹመቴ የማ
ገኘው ሳይኖር ወንጌልን ያለ ዋጋ እንዳስተምር
ባደርግ ነው።

### ብዙዎችን ስለ መጥቀም

፲፱እኔ ከሁሉ ይልቅ ነጻ ስሆን ብዙዎችን
ወደ ሃይማኖት እሰበስባቸው ዘንድ እንደ ባሪያ
ራሴን ለሁሉ አስገዛሁ። ፳አይሁድን እጠቅማ
ቸው ዘንድ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ ሆን
ሁላቸው፤ ከኦሪት በታች ያሉትን እጠቅም
ዘንድ እኔ ራሴ ከኦሪት በታች ሳልሆን ከኦ
ሪት በታች ላሉት ከኦሪት በታች እንዳለ ሰው
ሆንሁላቸው። ፳፩የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጋሁ
ሳልሆን፥ በክርስቶስ ሕግም ሳለሁ ሕግ የሌላቸ
ውን እጠቅማቸው ዘንድ ሕግ ለሌላቸው ሕግ
እንደሌለው ሆንሁላቸው። ፳፪ደካሞችንም እጠ
ቅማቸው ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ
ላቸው፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶቹን አድን
ዘንድ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ
ሆንሁ። ፳፫በወንጌልም ትምህርት አንድነት ይኖ
ረኝ ዘንድ ስለ ወንጌል ትምህርት ሁሉን አደ
ርጋለሁ።

፳፬በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሽቀዳደሙ
ሁሉ እንደሚፋጠኑ አታውቁምን? ለቀደመው
የሚደረግለት ዋጋ አለ፤ እንዲሁ እናንተም እን
ድታገኙ ፈጽማችሁ ሩጡ። ፳፭የሚታገል ሁሉ
በሁሉ ነገር ይታገሣል፤ እነርሱስ የሚጠፋው
ንና የሚያልፈውን የምስጋናቸውን ዋጋ አክ
ሊል ያገኙ ዘንድ ይበረታሉ፤ እኛ ግን የማያል
ፈውን አክሊል ለማግኘት እንታገሣለን። ፳፮እኔ
ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮ
ጥም፤ ነፋስንም እንደሚጐስም ሁሉ እንዲሁ
አልጋደልም። ፳፯ነገር ግን ለሌላ ሳስተምር፥
እኔ ለራሴ የተናቅሁ እንዳልሆን ሰውነቴን አስ
ጨንቃታለሁ፥ ሥጋዬንም አስገዛዋለሁ።

## ምዕራፍ ፲

### በእምነት ስለ አለመውደቅ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ አባቶቻችን ሁሉ
ደመና እንደ ጋረዳቸው ሁሉም በባሕር መካከል
አልፈው እንደ ሄዱ ልታውቁ እወዳለሁ። ፪ሁሉ
ንም ሙሴ በደመናና በባሕር አጠመቃቸው።[፲፩]
፫ሁሉም ያን መንፈሳዊ ምግብ ተመገቡ።
፬ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይኸ
ውም በኋላቸው ከሚሄደው ከመንፈሳዊ ዐለት
የጠጡት ነው፤ ያም ዐለት ክርስቶስ ነበረ።
፭እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሁሉም ደስ አላ
ለውም፤ ብዙዎቹ በምድረ በዳ ወድቀዋልና።
፮እነርሱ እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ ክፉ እንዳን
መኝ እነርሱ ለእኛ ምሳሌ ሆኑልን። ፯"እሕዛብ
ተቀመጡ፤ ይበሉና ይጠጡም ጀመር፤ ሊዘፍ
ኑም ተነሡ" ብሎ መጽሐፍ እንደ ተናገረ ከእ
ነርሱ አንዳንዶቹ እንደ አመለኩ ጣዖትን የምታ

---

፱ ግሪኩ "ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆነ እኛማ ይልቁን እንዴታ" ይላል።
፲ "ለቤተ እግዚአብሔር ሹሞች መተዳደሪያቸው የቤተ እግዚአብሔር መባ ነው" የሚለው በግሪኩ የለም።
፲፩ ግሪኩ "ሁሉም ከሙሴ ጋር አንድ ለመሆን በደመናና በባሕር ተጠመቁ" ይላል።

፱፥፲፩ ሮም ፲፭፥፳፯።    ፱፥፲፫ ዘዳ. ፲፰፥፩።    ፱፥፲፬ ማቴ. ፲፥፲፤ ሉቃ. ፲፥፯።
፲፥፩ ዘፀ. ፲፫፥፳፩-፳፪፤ ፲፬፥፳፪-፳፱።    ፲፥፫ ዘፀ. ፲፮፥፴፭።    ፲፥፬ ዘፀ. ፲፯፥፮፤ ዘኍ. ፳፥፪-፲፫።
፲፥፭ ዘኍ. ፲፬፥፳፱-፴።    ፲፥፮ ዘኍ ፲፩፥፬።    ፲፥፯ ዘፀ. ፴፪፥፮።

መልኩ አትሁኑ። ፰ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንደ
ሴሰኑ፥ በአንድ ቀንም ሃያ ሦስት ሺህ ሰዎች
እንደ ወደቁ አንሴስን። ፱ከእነርሱም አንዳንዶቹ
እግዚአብሔርን እንደ ተፈታተኑት፥ ነዘር እባ
ብም እንደ አጠፋቸው እግዚአብሔርን አንፈታ
ተን። ፲ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንዳንጐራጐሩ
በት፥ በመቅሠፍትም እንደጠፉ አናንጐራጕር።
፲፩እነርሱን ያገኛቸው ይህ ሁሉ ነገር በኋላ
ዘመን ለምንነሣው ለእኛ ትምህርትና ምክር
ሊሆነን ምሳሌ ሆኖ ተጻፈ። ፲፪አሁንም ያ ቆሚ
አለሁ ብሎ በራሱ የሚታመን ሰው እርሱ እን
ዳይወድቅ ይጠንቀቅ። ፲፫በሰው ላይ እንደሚደ
ርሰው ያለ ፈተና ነው እንጂ ሌላ ፈተና አያገኛ
ችሁም። በምትችሉት መከራ ነው እንጂ በማት
ችሉት መከራ ትፈተኑ ዘንድ ያልተዋችሁ እግ
ዚአብሔር የተመሰገነ ነው፤ እርሱም ከፈተና
ትድኑ ዘንድ በመከራ ጊዜ ይረዳችኋል።

## ከጣዖታት ስለ መራቅ

፲፬ወንድሞቼ! አሁንም ጣዖት ከማምለክ
ሽሹ። ፲፭ለዐዋቂዎች እንደሚነገር እነግራችኋ
ለሁ፤ ትክክለኛውንም እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ።
፲፮ይህ የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ
ደም ጋር አንድ አይደለምን? የምንፈትተው
ይህስ ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር አንድ አይ
ደለምን? ፲፯ኅብስቱ አንድ እንደ ሆነ እንዲሁ
እኛም ብዙዎች ስንሆን አንድ አካል ነን፤ ሁላ
ችን ከአንድ ኅብስት እንቀበላለንና። ፲፰እስራ
ኤል ዘሥጋን ተመልከቱ፤ መሥዋዕቱን ይበ
ላሉ፤ ከመሠዊያውም ጋር አንድ ይሆኑ አልነ
በረምን? ፲፱እንግዲህ ምን እንላለን? ለጣዖታት
የሚሠዋ መሥዋዕት ከንቱ ነው፤ ጣዖቶቻቸ
ውም ከንቱ ናቸው። ፳አሕዛብም የሚሠዉ ለአ
ጋንንት ነው እንጂ ለእግዚአብሔር አይደለም፤
ነገር ግን የአጋንንት ተባባሪዎች እንድትሆኑ
አልፈቅድላችሁም። ፳፩የእግዚአብሔርን ጽዋና
የአጋንንትን ጽዋ አንድ አድርጋችሁ መጠጣት
አትችሉም፤ የእግዚአብሔርን ማዕድና የአጋ
ንንትንም ማዕድ በአንድነት ልትበሉ አትች
ሉም። ፳፪እንግዲህ እግዚአብሔርን እናስቀና
ውን? በውኑ እኛ ከእርሱ እንበረታለን?

፳፫ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ነገር ግን ሁሉ የሚ
ጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፤ ነገር
ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። ፳፬ለባልንጀራ
ችሁ እንጂ ለራሳችሁ አታድሉ። ፳፭ደግሞም
በሥጋ ገበያ የሚሸጡትን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ
ሳትመራመሩ ብሉ። ፳፮"ምድር በመላዋ የእግዚ
አብሔር ናትና።" ፳፯ያላመነ ሰው ቢጠራችሁ፥
ልትሄዱም ብትወዱ ያቀረቡላችሁን ሁሉ ከሕ
ሊና የተነሣ ሳትመራመሩ ብሉ። ፳፰እንግዲህ
"ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው" ያላችሁ ቢኖር
ግን፥ ስለ ነገራችሁና ባልንጀራችሁም የሚጠ
ራጠር ስለሆነ አትብሉ። ፳፱ነጻነታችሁን እንዳ
ይነቅፉአት አስረድተዋችኋልና።[፭] ፴በጸጋ ብበላ
ግን በነገሩ ስለማመስግን ስምን ይነቅፉኛል?
፴፩ብትበሉም፥ ብትጠጡም የምታደርጉትን
ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። ፴፪ለአ
ይሁድም፥ ለአረማውያንም፥ ለእግዚአብሔር
ቤተ ክርስቲያንም ያለ ማሰናከል እርእያ ሁኑ
እቸው። ፴፫እኔም ሁሉን በሁሉ ነገር ደስ እን
ዳሰኝ ይድኑ ዘንድ የብዙዎችን ተድላ እሻለሁ
እንጂ የራሴን ተድላ የምሻ አይደለሁምና።

## ምዕራፍ ፲፩

### የመምህራንን ፍለጋ መከተል

፩እኔ ክርስቶስን እንደምመስለው እኔን
ምሰሉ።
፪ወንድሞቼ ሆይ፥ አመሰግናችኋለሁ፤ ዘወ
ትር ታስቡኛላችሁና፤ ያስተማርኋችሁንም ትም
ህርት ጠብቃችኋልና። ፫ነገር ግን የወንድ ሁሉ
ራሱ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስዋ ወንድ፤ የክርስ
ቶስም ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ
እወድዳለሁ።

### የጸሎት ሥርዐት

፬ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም የሚያስ
ተምር ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል። ፭ራስዋን
ሳትከናነብ የምትጸልይ ወይም የምታስተምር
ሴት ሁላ ራስዋን ታዋርዳለች፤ ራስዋን እንደ
ተላጨች መሆንዋ ነውና። ፮ሴት ካልተከናነበች
ትላጭ ወይም ጠጕርዋን ትቈረጥ፤ ለሴት ጠጕ

---

፭ ምዕ. ፲ ቍ. ፳፱ ግሪኩ "ስለ ባልንጀራህ ሕሊና እንጂ ስለገዛ ሕሊናህ አልናገርም፤ ነጻነቴ በሌላ ሰው ሕሊና የሚፈ
ርድ ስለምን ነው?" ይላል።

፲፥፰ ዘኍ. ፳፭፥፩-፲፰። ፲፥፱ ዘኍ. ፳፩፥፭-፮። ፲፥፲ ዘኍ. ፲፮፥፵፩-፵፱።
፲፥፲፮ ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፰፤ ማር. ፲፬፥፳፪-፳፬፤ ሉቃ. ፳፪፥፲፱-፳። ፲፥፲፰ ዘሌ. ፯፥፮። ፲፥፳ ዘዳ. ፴፪፥፲፯።
፲፥፳፪ ዘዳ. ፴፪፥፳፩። ፲፥፳፫ ፩ቆሮ. ፮፥፲፪። ፲፥፳፮ መዝ. ፳፬፥፩። ፲፩፥፩ ፩ቆሮ. ፬፥፲፮፤ ፊል. ፫፥፲፯።

ርዋን መቈረጥ ወይም መላጨት ውርደት ከሆነ
ትከናነብ። ፯ወንድ በሚጸልይበት ጊዜ[፩] ሊከና
ነብ አይገባውም፤ የእግዚአብሔር አርአያውና
እምሳሉ[፪] ነውና፤ ሴትም ለባልዋ ክብር ናት።
፰ሴት ከወንድ ተገኝታለችና፤ ወንድ ግን ከሴት
የተገኘ አይደለም። ፱ወንድ ስለ ሴት አልተፈጠ
ረም፤ ሴት ስለ ወንድ ተፈጠረች እንጂ። ፲ስለ
ዚህም ሴት ስለ መላእክት፥ ሥልጣን ለራስዋ
ሊሆን ይገባል፤[፫] ፲፩ነገር ግን አሁን ሴት ከባሏ
እትለይ፤ ወንድም ከሚስቱ አይለይ፤ ሁላች
ሁም በጌታችን ኑሩ።[፬] ፲፪ሴት ከወንድ እንደ
ተገኘች እንዲሁ ወንድ ከሴት ተገኘ፤ ነገር ግን
ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ፲፫እስኪ እናንተ
ራሳችሁ ፍረዱ፤ ሴት ወደ እግዚአብሔር በም
ትጸልይበት ጊዜ ልትከናነብ አይገባምን? ፲፬ተፈ
ጥሮዋስ አያስረዳችሁምን? ወንድ ግን ጠጕሩን
ቢያሳድግ ነውር ነው። ፲፭ለሴት ግን ጠጕርዋን
ብታሳድግ ክብርዋ ነው፤ ለሴት ጠጕርዋ እንደ
ቀጸላ ሆኖ ተሰጥቶአታልና። ፲፮ነገር ግን የሚጠ
ራጠር ቢኖር እኛ ወይም የእግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያን እንዲህ ያለ ልማድ የለንም።

## ጸብና ክርክር እንደማይገባ

፲፯ይህንም የነገርኋችሁ ላመስግናችሁ አይ
ደለም፤ በምትሰበሰቡበት ጊዜ ወደ ዝቅተኛ
እንጂ ወደሚሻል ግብር አትሄዱምና። ፲፰ከሁሉ
አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን በምትሰበሰቡ ጊዜ
እንደምትጣሉና እንደምትከራከሩ ሰምቻለሁ፤
የማምነውም አለኝ። ፲፱ከእናንተ የተመረጡት
ወንድሞች ተለይተው እንዲታወቁ ትለያዩ
ዘንድ ግድ ነው። ፳እንግዲህ እናንተም በምት
ሰበሰቡበት ጊዜ የምትበሉና የምትጠጡ ለጌታ
ችን ቀን[፭] እንደሚገባ አይደለም። ፳፩ወደ ምግብ
ትሽቀዳደማላችሁ፤ የተራቡ በአጠገባችሁ እያሉ
እናንተ ትበላላችሁ፤ ትጠግባላችሁ፤ ትስክራ
ላችሁም።[፮] ፳፪በውኑ የምትበሉበትና የምትጠ
ጡበት ቤት የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔ
ርን ቤተ ክርስቲያን ታስነቅፋላችሁን? ነዳያን
ንስ ታሳፍሩአቸዋላችሁን? ምን እላለሁ? በዚህ
አመሰግናችኋለሁን? አላመሰግናችሁም።

## ስለ ጌታችን ሥጋና ደም

(ማቴ. ፳፮፥፳፮-፳፱፤ ማር. ፲፬፥፳፪-፳፭)

፳፫ከእግዚአብሔር እንደ ተማርሁ አስተምሬ
አችኋለሁና፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እር
ሱን ራሱን በያዙባት በዚያች ሌሊት ኅብስቱን
አነሣ። ፳፬አመሰገነ፤ ባረከ፤[፯] ፈተተ፤ እንዲህም
አላቸው፥ "እንኩ ብሉ፤ ስለ እናንተ የሚሰ
ጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ መታሰቢያዬንም እን
ዲሁ አድርጉ።" ፳፭እንዲሁም ኅብስቱን ከተ
ቀበሉ በኋላ ጽዋውን አንሥቶ፥ "አዲስ ሥር
ዐት የሚጸናበት ይህ ጽዋ ደሜ ነው እንዲህ
አድርጉ፤ በምትጠጡበትም ጊዜ አስቡኝ" አላ
ቸው። ፳፮ይህን ኅብስት በምትበሉበት፥ ይህንም
ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ጌታችን እስከሚ
መጣበት ቀን ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ።
፳፯እሁንም ሳይገባው ይህን ኅብስት የበላ፥
ይህንም ጽዋ የጠጣ የጌታችን ሥጋውና ደሙ
ስለሆነ ዕዳ አለበት። ፳፰አሁንም ሰው ራሱን
መርምሮና አንጽቶ ከዚህ ኅብስት ይብላ፤ ከዚ
ህም ጽዋ ይጠጣ። ፳፱ሳይገባው፥ የጌታችን
ሥጋም እንደ ሆነ ሳያውቅ፥ ሰውነቱንም ሳያ
ነጻ፥[፰] የሚበላና የሚጠጣ ለራሱ ፍርዱንና መቅ
ሠፍቱን ይበላል፤ ይጠጣልም። ፴ስለዚህ ከመካ
ከላችሁ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች ናቸው፤
ብዙዎችም በድንገት አንቀላፍተዋል። ፴፩እኛ
በራሳችን ብንፈርድ ኖሮ ባልተፈረደብንም
ነበር። ፴፪ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም
ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን።
፴፫እሁንም ወንሞቻችን ሆይ፥ ለምሳ በም
ትሰበሰቡበት ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ፤
፴፬መሰብሰባችሁ ለፍዳ እንዳይሆን፥ የተራበ

---

፩ "በሚጸልይበት ጊዜ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፪ ግሪኩ "አርአያውና ክብሩ" ይላል።
፫ ምሥጢሩ ትከናነብ ማለት ነው።
፬ ግሪኩ "... በጌታ ዘንድ ሴት ያለወንድ ወንድም ያለሴት አይሆንም" ይላል።
፭ ግሪኩ "የጌታን እራት የምትበሉ አይደለም" ይላል።
፮ ምዕ. ፲፩ ቍ. ፳፩ ግሪኩ "በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክ
ራል" ይላል።
፯ "ባረከ" የሚለው በግሪኩ የለም።
፰ "ሰውነቱንም ሳያነጻ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፩፥፯ ዘፍ. ፩፥፳፮-፳፯። ፲፩፥፰-፱ ዘፍ. ፪፥፲፰-፳፫። ፲፩፥፳፭ ዘፀ. ፳፬፥፮-፰፤ ኤር. ፴፩፥፴፩-፴፬።

ቢኖር በቤቱ ይብላ፤ አትንቃቀፉም፤[፱] ሌላውን
ሥርዐት ግን መጥቼ እሠራላችኋለሁ።

## ምዕራፍ ፲፪

### ከመንፈስ ቅዱስ ስለሚገኙ ሀብታት

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ
ስጦታም ታውቁ ዘንድ እንጂ አላዋቆች ልት
ሆኑ አንወድድም። ፪ቀድሞም እናንተ አሕዛብ
በነበራችሁ ጊዜ ዲዳዎች ጣዖታትን ታመልኩ
እንደ ነበር፥ ጣዖትም በማምለክ ረክሳችሁ እንደ
ነበር፥[፩] ወደ ወሰዱአችሁም ትሄዱ እንደ ነበር
ታውቃላችሁ። ፫ስለዚህም ማንም በእግዚአብ
ሔር መንፈስ ሲናገር፥ “ኢየሱስ ውጉዝ ነው”
የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ
በቀር “ኢየሱስ ጌታ ነው” ሲል አንድስ እን
ኳን እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።
፬መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ስጦታው ልዩ
ልዩ ነው። ፭ጌታም አንድ ሲሆን ልዩ ልዩ አገ
ልግሎቶች አሉ። ፮ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ
እግዚአብሔርም አንድ ሲሆን ልዩ ልዩ አሠ
ራር አለ። ፯ለሁሉም ጌታ እየረዳ በየዕድሉ
እንደሚገባውና እንደሚጠቅመው ለእያንዳንዱ
በግልጥ ይሰጠዋል፤ ፰በመንፈስ ቅዱስ የጥበብ
ቃል የሚሰጠው አለ፤ በመንፈስ ቅዱስም የዕ
ውቀት ቃል የሚሰጠው አለ። ፱ለአንዱም በዚ
ያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም በአንዱ መን
ፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ፲ለአንዱም ተአምራትን
ማድረግ፥ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአን
ዱም መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ
ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች
የተነገረውን መተርጐም ይሰጠዋል። ፲፩በዚህም
ሁሉ ያው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ይረ
ዳል፤ ለሁሉም እንደ ወደደ ያድላቸዋል።
፲፪አካል አንድ እንደ ሆነ ብዙ የአካል ክፍሎ
ችም እንደ አሉበት፥ ነገር ግን የአካል ክፍሎች
ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ ክር
ስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው፤ ፲፫እኛ ሁላችንም
በአንድ መንፈስ አንድ አካል ለመሆን ተጠም
ቀናል፤ አይሁድ ብንሆን፥ አረማውያንም ብን
ሆን፥ ባሪያዎችም ብንሆን፥ ነጻዎችም ብንሆን
ሁላችን አንድ መንፈስን ጠጥተናልና። ፲፬የአካ
ላችንም ክፍሉ ብዙ ነው እንጂ አንድ አይደ
ለም። ፲፭እግርም፥ “እኔ እጅ አይደለሁምና የአ
ካል ክፍል አይደለሁም” ብትል ይህን በማለቷ
የአካል ክፍል መሆንዋ ይቀራልን? ፲፮ጆሮም፥
“እኔ ዐይን አይደለሁምና የአካል ክፍል አይ
ደለሁም” ብትል ይህን በማለቷ የአካል ክፍል
መሆንዋ ይቀራልን? ፲፯አካል ሁሉ ዐይን ቢሆን
ኖሮ መስማት ከየት በተገኘ ነበር፤ አካልስ ሁሉ
ጆሮ ቢሆን ኖሮ ማሽተት ከየት በተገኘ ነበር?
፲፰አሁን ግን እግዚአብሔር የአካላችንን ክፍል
በሰውነታችን ውስጥ እርሱ እንደ ወደደ እየራሱ
አከናውኖ መደበው። ፲፱የአካል ክፍሉ አንድ
ቢሆን ኖሮ አካል የት በተገኘ ነበር? ፳አሁንም
የአካል ክፍሎች ብዙዎች ናቸው፤ አካሉ ግን
አንድ ነው። ፳፩ዐይን እጅን፥ “አልፈልግሽም”
ልትላት አትችልም፤ ራስም፥ “እግሮችን አል
ፈልጋችሁም” ልትላቸው አትችልም። ፳፪ደካ
ሞች የሚመስሉህ የአካል ክፍሎች ይልቁን
የሚያስፈልጉህ ናቸው። ፳፫ከአካልም ክፍሎች
የተናቁ ለሚመስሉን ክብርን እንጨምርላቸዋ
ለን፤ ለምናፍርባቸውም የአካል ክፍሎች ክብር
ይጨመርላቸዋል። ፳፬ለከበረው የአካላችን ክፍል
ክብርን አንሻለትም፤ እግዚአብሔር ግን ሰው
ነታችንን አስማምቶታል፤ ይልቁንም ታናሹን
የአካል ክፍል አክብሮታል። ፳፭የአካላችን ክፍ
ሎች እርስ በርሳቸው እንዳይለያዩ፥ አካላችን
ሳይነጣጠል በክብር እንዲተካከል አስማማው።
፳፮አንዱ የአካል ክፍል ቢታመም ከእርሱ ጋር
የአካል ክፍሎች ሁሉ ይታመማሉ፤ አንዱ የአ
ካል ክፍል ደስ ቢለውም[፪] የአካል ክፍሎች
ሁሉ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል። ፳፯እንግዲህ
እናንተ የክርስቶስ አካሉ ናችሁ፤ እያንዳንዳች
ሁም የአካሉ ክፍሎች ናችሁ። ፳፰እግዚአብሔር
ለቤተ ክርስቲያን የሾማቸው አስቀድሞ ሐዋርያ
ትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥ ሦስተኛም መምህ
ራንን፥ ከዚህም በኋላ ተአምራትና ኀይል ማድ
ረግ የተሰጣቸውን፥ ቀጥሎም የመፈወስ ሀብት
የተሰጣቸውን፥ የመርዳትም ሀብት የተሰጣቸ
ውን፥ የመምራትና ቋንቋን የመናገር ሀብት
የተሰጣቸውን ነው። ፳፱በውኑ ሁሉ ሐዋርያትን
ይሆናሉን? ሁሉስ ነቢያትን ይሆናሉን? ሁሉስ
መምህራንን ይሆናሉን? ለሁሉስ ተአምራትን

---

፱ “አትንቃቀፉም” የሚለው በግሪኩ የለም።

፩ “ጣዖትም በማምለክ ረክሳችሁ እንደ ነበረ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ በግሪኩ “ቢከብርም” ይላል።

፲፪፥፩-፲፩ ሮም ፲፪፥፮-፰። ፲፪፥፲፪ ሮም ፲፪፥፬-፭። ፲፪፥፳፰ ኤፌ. ፬፥፲፩።

የማድረግ ኀይል ይሰጣልን? ፴ለሁሉስ የመፈ
ወስ ህብት ይሰጣልን? ሁሉስ በቋንቋ ይናገራ
ሉን? ሁሉስ ይተረጕማሉን? ፴፩ነገር ግን ለም
ትበልጠው ጸጋ ቅኑ፤ ደግሞም የምትሻለውን
መንገድ አስተምራችኋለሁ።

## ምዕራፍ ፲፫

### ስለ ፍቅር

፩የሰውን ሁሉ ቋንቋ ባውቅ፥ የመላእክትንም
ሁሉ ቋንቋ ባውቅ፥ ነገር ግን ፍቅር ከሌለኝ
እንደሚጮህ ነሐስ፥ ወይም እንደሚመታ ከበሮ[፩]
መሆኔ ነው። ፪ትንቢት ብናገር፥ የተሰውረውን
ሁሉ፥ ጥበብንም ሁሉ ባውቅ፥ ተራራ እስከ
ማፍለስ የሚያደርስ ፍጹም እምነትም ቢኖረኝ
ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ፫ገንዘቤን ሁሉ ለም
ጽዋት ብሰጥ፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል
ብሰጥ፥ ነገር ግን ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይ
ጠቅመኝም።

፬ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤
ፍቅር አያቀናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር
ልቡናን አያስታብይም። ፭ብቻዬን ይድላኝ አያ
ሰኝም፤[፪] አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርንም አያሳስ
ብም። ፮ጽድቅን በመሥራት ደስ ያሰኛል እንጂ፥
ግፍን በመሥራት ደስ አያሰኝም። ፯በሁሉ ያቻ
ችላል፤ በሁሉም ያስተማምናል፤ በሁሉም
ተስፋ ያስደርጋል፥ በሁሉም ያስታግሣል።

፰ፍቅር ለዘወትር አይጥልም፤ ትንቢት የሚና
ገርም ያልፋል፤ ይሻራልም፤ በልዩ ልዩ ቋንቋ
የሚናገርም ያልፋል፤ ይቀራል፤ የሚራቀቅም
ያልፋል፤ ይጠፋል።[፫] ፱በየገጹ ጥቂት ጥቂት
እናውቃለንና፤ ጥቂት ጥቂት ትንቢትም እንና
ገራለንና። ፲ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ያ ተከ
ፍሎ የነበረው ይሻራል። ፲፩እኔ ልጅ በነበርሁ
ጊዜ እንደ ልጅ እናገር ነበር፤ እንደ ልጅም
አስብ ነበር፤ እንደ ልጅም እመከር ነበር፤ በአ
ደግሁ ጊዜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሁሉ ሻርሁ።
፲፪አሁን ግን ታወቀኝ፤ በግልጥም ተረዳኝ፤[፬]
በመስታወትም እንደሚያይ ሰው ዛሬ በድንግዝ
ግዝታ እናያለን፤ ያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እና
ያለን፤ አሁን በከፊል፥ ኋላ ግን እንደ ተገለጠ
ልኝ መጠን ሁሉን አውቃለሁ። ፲፫አሁንም እነ
ዚህ ሦስቱ እምነት፥ ተስፋና ፍቅር ጸንተው
ይኖራሉ፤ ከሁሉ ግን ፍቅር ይበልጣል።

## ምዕራፍ ፲፬

### በቋንቋ ስለ መናገርና ስለ መተርጐም ህብት

፩ፍቅርን ተከተሏት፤ ለመንፈሳዊ ስጦታ፥
ይልቁንም ትንቢት ለመናገር ተፎካከሩ። ፪በቋ
ንቋ የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው የሚ
ናገር አይደለም። የሚናገረውን የሚሰማው የለ
ምና፥ ነገር ግን በመንፈስ ምሥጢርን ይናገ
ራል። ፫ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመ
ምከር፥ ለማረጋጋትም ለሰው ይናገራል። ፬በቋ
ንቋ የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ የሚተረጕም ግን
የክርስቲያን ማኅበርን ያንጻል። ፭ሁላችሁም በቋ
ንቋ ልትናገሩ እወዳለሁ፤ ይልቁንም ትንቢት
ልትናገሩ እወዳለሁ፤ ሳይተረጕም በቋንቋ ከሚ
ናገር ይልቅ ትንቢት የሚናገር እጅግ ይበልጣ
ልና፤ ቢተረጕም ግን ማኅበሩን ያንጻል።

፮አሁንም ወንድሞቼ ሆይ፥ ወደ እናንተ
መጥቼ በማታውቁት ቋንቋ ባነጋግራችሁ፥
የጥበብ ነገርንም ቢሆን፥ የትንቢትንም ነገር
ቢሆን፥ የማስተማር ሥራንም ቢሆን ገልጬ
ካልነገርኋችሁ የምጠቅማችሁ ጥቅም ምንድን
ነው? ፯ነፍስ የሌለው ድምፅ የሚሰጥ እንደ
መሰንቆ፥[፭] ወይም እንደ ክራር ያለ መሣሪያ
በስልት ካልተመታ መሰንቆው ወይም ክራሩ
የሚለውን ማን ያውቃል? ፰መለከት የሚነ
ፋም በታወቀው ስልት ካልነፋ ለጦርነት ማን
ይዘጋጃል? ፱እንዲሁም እናንተ በማይታወቅ
ቋንቋ ብትናገሩ፥ ይህንኑም ገልጣችሁ ባት
ተረጕሙ የምትሉትንና የምትናገሩትን ማን
ያውቃል? ከነፋስ ጋር እንደምትነጋገሩ ትሆ
ናላችሁ። ፲በዓለም ልዩ ልዩ ቋንቋዎች አሉ፤

---

፩ ግሪኩ "እንደሚንሿሿው ጸናጽል" ይላል።

፪ ግሪኩ "የማይገባውን አያደርግም" ይላል።

፫ ምዕ. ፲፫ ከቍ. ፬ እስከ ፰ ግሪኩ የነገሩን ስም እንደ ሰብእዊ በማድረግ "ፍቅር ይታገሣል ... ፍቅር ለዘወትር አይ
ወድቅም ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ ዕውቀትም ቢሆን ይቀራል" ይላል።

፬ "ታወቀኝ በግልጥም ተረዳኝ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፭ ግሪኩ "እንደ ዋሽንት" ይላል።

፲፫፥፪ ማቴ. ፲፯፥፳፤ ፳፩፥፳፩፤ ማር. ፲፩፥፳፫። ፲፫፥፭ ፊል. ፪፥፬። ፲፫፥፲፫ ፩ ተሰ. ፩፥፫።
፲፬፥፭ ዘኍል. ፲፩፥፳፱።

ከእነርሱም ትርጒም የሌለው አንድም የለም።
፲፩የቋንቋውን ትርጓሜ ካላወቅሁ እኔ ለሚያ
ነጋግረኝ እንደ እንግዳ እሆንበታለሁ፤ የሚ
ያነጋግረኝ እርሱም ለእኔ እንደ እንግዳ ይሆ
ናል። ፲፪እንዲሁ እናንተም ለመንፈስ ቅዱስ
ስጦታ ተፎካከሩ፤ ትበዙም ዘንድ ማኅበሩ
የሚታነጽበትን ፈልጉ። ፲፫በማያውቀው ቋንቋ
የሚናገር ሰውም መተርጐም እንዲችል ይጸ
ልይ። ፲፬በማላውቀው ቋንቋ የምጸልይ ከሆ
ንሁ ቃሌ ብቻ ይጸልያል፤ ልቤ ግን ባዶ
ነው። ፲፭እንግዲህ ምን አደርጋለሁ በመን
ፈስ እጸልያለሁ፤ በማስተዋልም እማልዳለሁ፤
በመንፈሴ እዘምራለሁ፤ በማስተዋልም እዘም
ራለሁ። ፲፮አንተ በመንፈስ ብታመሰግን፥ ያ
የቆመው ያልተማረው በአንተ ምስጋና ላይ
እንዴት አሜን ይላል? የምትናገረውንና የም
ትጸልየውን አያውቅምና። ፲፯እነሆ፥ አንተስ
መልካም ታመሰግናለህ፤ ነገር ግን ሌላው
እንዴት ይታነጻል? ፲፰እግዚአብሔርን አመሰ
ግነዋለሁ፤ ከሁላችሁ ይልቅ እኔ በቋንቋዎች
እናገራለሁና። ፲፱ነገር ግን ሌሎችን አስተምር
ዘንድ፥ በቋንቋ ከሚነገር ብዙ ቃል ይልቅ
በቤተ ክርስቲያን በአእምሮዬ አምስት ቃላ
ትን ልናገር እሻለሁ።

፳ወንድሞቻችን ሆይ፥ በአእምሮ እንደ ሕፃ
ናት አትሁኑ፤ ነገር ግን ለክፉ ነገር እንደ
ሕፃናት ሁኑ፤ በዕውቀትም ፍጹማን ሁኑ።
፳፩በኦሪትም፥ "ይህን ሕዝብ በሌሎች ቋንቋ
ዎችና በሌላ አንደበት እናገራቸዋለሁ፤ እን
ዲሁም ሆኖ አይሰሙኝም ይላል እግዚአብ
ሔር" ተብሎአል። ፳፪አሁንም ቋንቋ መና
ገር ለማያምኑ ሰዎች ለምልክት ነው፤ ለሚ
ያምኑ ግን አይደለም፤ ትንቢትም ለሚያምኑ
ነው እንጂ ለማያምኑ አይደለም። ፳፫ሕዝቡ
ሁሉ በአንድነት ቢሰበሰቡ፥ ሁሉም በልዩ
ልዩ ቋንቋ ቢናገሩ፥ አላዋቂዎች፥ ወይም
የማያምኑ ቢመጡ አብደዋል ይሉአቸው የለ
ምን? ፳፬ሁሉም ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያ
ምኑ ወይም አላዋቂዎች ቢመጡ ሁሉ ይከ
ራከሩአቸው የለምን? ሁሉስ ያሳፍሩአቸው
የለምን? ፳፭በልባቸው የደበቁትም ይገለጣል፤
ከዚህ በኋላ ያ የማያምነው ተመልሶ ይጸ
ጸታል፤ በግንባሩም ወድቆ ለእግዚአብሔር
ይሰግዳል፥ በእውነት እግዚአብሔር ከእናንተ
ጋር እንዳለም ይናገራል።

## ስለ ጸሎተ ማኅበር ሥርዐት

፳፮አሁንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ሁላችሁ
በምትሰበሰቡበት ጊዜ መዝሙር አላችሁ፤ ትም
ህርት አላችሁ፤ መግለጥ አላችሁ፤ በቋንቋ መና
ገር አላችሁ፤ መተርጐምም አላችሁ፤ ሁሉም
ለሚታነጽበት ጥቅም አድርጉት። ፳፯በቋንቋ የሚ
ናገር ቢኖር ሁለት ሁለት፥ ወይም ቢበዛ ሦስት
ሦስት እየሆኑ በተራ ይናገሩ፤ ሌላውም ይተር
ጒምለት። ፳፰የሚተረጒም ከሌለ ግን በቤተ ክር
ስቲያን በቋንቋ የሚናገረው ዝም ይበል፤ በእ
ግዚአብሔር መካከልና በእርሱ መካከል ይና
ገር። ፳፱ነቢያትም ቃላቸው ለቤተ ክርስቲያን
ይታወቅ ዘንድ ሁለት ሁለት፥ ወይም ሦስት
ሦስት ሆነው ይናገሩ። ፴ተቀምጦ ሳለ ምሥ
ጢር የተገለጠለት ቢኖር ፊተኛው ዝም ይበል።
፴፩ሁሉ እንዲማር፥ ሁሉም ደስ እንዲለው፥ እን
ዲጸናም ሁላችሁ እያንዳንዳችሁ ትንቢት ልት
ናገሩ ትችላላችሁና። ፴፪የነቢያት ሀብት ለነቢ
ያት ይለጣልና። ፴፫በቅዱሳን ጉባኤ ሁሉ እንደ
ሚደረግ፥ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ
የሁከት አምላክ አይደለምና። ፴፬ሴቶችም በቤተ
ክርስቲያን ዝም ይበሉ፤ ሊታዘዙ እንጂ ሊና
ገሩ አልተፈቀደምና፤ ኦሪትም እንዲህ ብሎአ
ልና። ፴፭ለሴት በቤተ ክርስቲያን መናገር ክል
ክል ነው፤ ሊማሩ ከወደዱ ደግሞ በቤታቸው
ባሎቻቸውን ይጠይቁ። ፴፮የእግዚአብሔር ቃል
ከእናንተ ብቻ ወጥቶአልን? ወይስ የእግዚአብ
ሔር ቃል ወደ እናንተ ብቻ ደርሶአልን?

፴፯ራሱን እንደ ነቢይ አድርጎ ወይም መንፈስ
ቅዱስ እንዳደረበት አድርጎ የሚቈጥር ቢኖር፥
የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነውና ይህን የጻፍሁላ
ችሁን ይወቅ። ፴፰ነገር ግን ይህን የማያውቅ
ቢኖር እግዚአብሔርን አያውቀውም። ፴፱አሁ
ንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ትንቢትን ለመናገር
ቅኑ፤ በቋንቋ የሚናገረውንም አትከልክሉት።
፵ነገር ግን ሁሉን በአገባብና በሥርዐት አድ
ርጉ፤

## ምዕራፍ ፲፭

## የተማሩትን ስለ ማስታወስ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ ያስተማርኋችሁንና የተ
ቀበላችሁትን ያላችሁበትን፥ በእርሱም የምትድ
ኑበትን ወንጌል አሳስባችኋለሁ። ፪ያስተማርኋች

---

፲፬፥፳ ኤፌ. ፬፥፲፬፥፲፱። ፲፬፥፳፩ ኢሳ. ፳፰፥፲፩-፲፪።

ሁን ታስቡ እንደ ሆነ በቃሌ አስተምሬአችኋ
ለሁ፤ ያለዚያ ግን ማመናችሁ ከንቱ ነው።

## ስለ ጌታችን ትንሣኤና መገለጥ

፫እኔ የተማርሁትን አስቀድሜ መጽሐፍ እን
ደሚል እንዲህ ብዬ አስተማርኋችሁ፥ “ክርስ
ቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ። ፬ተቀበረ፤ እንደ
ተጻፈም በሦስተኛው ቀን ተነሣ።” ፭ለጴጥሮስ
ታየው፤ ከዚህም በኋላ ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛ
ሙርቱ ታያቸው። ፮ከዚህም በኋላ ከአምስት
መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታያ
ቸው፤ ከእነርሱ ብዙዎቹ እስከ ዛሬ አሉ፤ አንዳ
ንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል። ፯ከዚህም በኋላ ለያ
ዕቆብ ታየው፤ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ፤ ፰ከሁ
ሉም በኋላ ጭንጋፍ ለምመስል ለእኔ ታየኝ።
፱ከሐዋርያት ሁሉ እኔ አንሣለሁና፤ የእግዚአ
ብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስለ አሳደድሁ ሐዋ
ርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፥ ፲ነገር ግን በእ
ግዚአብሔር ጸጋ አሁን እኔ ባለሁበት አለሁ፤
ለእኔም የሰጠኝ ጸጋው ለከንቱ የሆነብኝ አይ
ደለም፤ እኔም ከሁሉ ይልቅ ደከምሁ፤ ነገር
ግን በእኔ ላይ ያደረው የእግዚአብሔር ጸጋ አጸ
ናኝ እንጂ እኔ አይደለሁም። ፲፩አሁንም እኔም
ብሆን፥ እነርሱም ቢሆኑ እንዲህ እናስተምራ
ለን፤ እናንተም እንዲሁ አምናችኋል።

## ስለ ሙታን መነሣት

፲፪ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶአል
ብለን ለሌላው የምናስተምር ከሆነ፥ እንግዲህ
ከመካከላችሁ ሙታን አይነሡም የሚሉ እን
ዴት ይኖራሉ? ፲፫ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክር
ስቶስም ከሙታን ተለይቶ አልተነሣማ፤ ፲፬ክርስ
ቶስም ከሙታን ካልተነሣ እንግዲያስ ትምህርታ
ችን ከንቱ ነው፤ የእናንተም እምነታችሁ ከንቱ
ነው። ፲፭እኛም በእግዚአብሔር ላይ የሐሰት
ምስክሮች ሆነናል፤ ክርስቶስን አስነሣው ብለና
ልና፥ እንግዲያ ሳያስነሣው ነውን?። ፲፮ሙታን
የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስም ከሙታን አልተነ
ሣማ። ፲፯ክርስቶስም ከሙታን ካልተነሣ ማመ
ናችሁ ከንቱ ነው፤ ገናም በኀጢአታችሁ አላ
ችሁ። ፲፰እንግዲያስ በክርስቶስ አምነው የሞቱ
ጠፍተዋላ። ፲፱በዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ክር
ስቶስን ተስፋ ከአደረግነው ከሰው ሁሉ ይልቅ
ጐስቋሎች ነን።

፳አሁንም ክርስቶስ ከሞቱ ሰዎች ሁሉ አስቀ
ድሞ ተነሥቶአል። ፳፩በመጀመሪያው ሰው ሞት
መጥቶአልና፥ በሁለተኛው ሰው ትንሣኤ ሙታን
ሆነ። ፳፪ሁሉ በአዳም እንደሚሞት እንዲሁ በክር
ስቶስ ሁሉ ሕያዋን ይሆናሉ። ፳፫ነገር ግን ሰው
ሁሉ በየሥርዐቱ ይነሣል፤ በመጀመሪያ ከሙታን
የተነሣ ክርስቶስ ነው፤ ከዚያ በኋላ በክርስቶስ
ያመኑ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ ይነሣሉ። ፳፬እግ
ዚአብሔር አብ መንግሥቱን እጅ ባደረገ ጊዜ፥
ገዥም ሁሉ፥ ንጉሥም ሁሉ፥ ኀይልም ሁሉ
በተሻረ ጊዜ፥ ያንጊዜ ፍጻሜ ይሆናል። ፳፭ጠላ
ቶቹ ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪወድቁ[፩] ድረስ ይነ
ግሥ ዘንድ አለውና። ፳፮ከዚያ በኋላ የመጨረሻው
ጠላት ይሻራል፤ ይኸውም ሞት ነው። ፳፯ሁሉን
ከእግሩ በታች አስገዝቶለታልና፥ “ሁሉ ይገዛለት”
ባለ ጊዜ ግን ሁሉን ከሚያስገዛለት በቀር እንደ ሆነ
የታወቀ ነው። ፳፰ሁሉም በተገዛለት ጊዜ ግን እግ
ዚአብሔር በሁሉ ቦታ በሁሉ ይሆን ዘንድ፥ ያን
ዕለት ወልድም ሁሉን ሳስገዛለት ይገዛል።

፳፱ያለዚያማ ለምን ያጠምቃሉ? ሙታን እንዲ
ነሡ አይደለምን? ሙታን የማይነሡ ከሆነስ ለምን
ያጠምቃሉ?[፪] ፴እንግዲህ እኛስ ሁልጊዜ መከራን
ስለምን እንቀበላለን? ፴፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነውና በእናንተ ላይ
ባለኝ ትምክህት ሁልጊዜ እገደላለሁ። ፴፪በውኑ
በኤፌሶን ከአውሬ ጋር የታገልሁ ለሰው ብዬ
ነውን? ምንስ ይጠቅመኛል? ሙታን የማይነሡ
ከሆነ እንግዲህ እንብላ እንጠጣ፥ ነገም እንሞታ
ለን። ፴፫ወንድሞቻችን[፫] አያስቱአችሁ፤ ክፉ ነገር
መልካም ጠባይን ያበላሻልና።

## ስለ ትንሣኤ በምሳሌ ትምህርት

፴፬ለጽድቅ ትጉ፤ አትሳቱ፤ እግዚአብሔርን
የማያውቁት ሰዎች አሉና፤ ነገር ግን እንድታ

---

፩ ግሪኩ “ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪጥልለት ድረስ” ይላል።

፪ ግሪኩ “እንግዲያማ ካልሆነ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ ስለ እነርሱ የሚ ጠመቁ ስለ ምንድን ነው?” ይላል።

፫ “ወንድሞቻችን” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፭፥፫ መዝ. ፳፩፥፭-፲፪። ፲፭፥፬ መዝ. ፲፭፥፰-፲፤ ማቴ. ፲፪፥፵፤ ሐ.ሥ. ፪፥፳፬-፴፪። ፲፭፥፭ ማቴ. ፳፰፥፲፮-፲፯፤ ማር. ፲፮፥፲፬፤ ሉቃ. ፳፬፥፴፬፤ ፴፮፥ ዮሐ. ፳፥፲፱። ፲፭፥፰ ሐ.ሥ. ፱፥፫-፮። ፲፭፥፱ ሐ.ሥ. ፰፥፫። ፲፭፥፳፭ መዝ. ፻፱፥፩። ፲፭፥፳፯ መዝ. ፰፥፮። ፲፭፥፴፪ ኢሳ. ፳፪፥፲፫።

ፍሩ ይህን እሳችኋለሁ፤ ፴፭ሙታን እንዴት ይነ
ሣሉ? የሚነሡስ በምን አካላቸው ነው? የሚል
አለ። ፴፮አንተ ስነፍ! አንተ የምትዘራው እን
ኳን ካልፈረሰ አይበቅልም። ፴፯የምትዘራውም
የስንዴ ቢሆን፥ የሌላም ቢሆን የምትዘራት ቅን
ጣት ብቻ ናት እንጂ ይህ ኋላ የሚገኘው አገ
ዳው አይደለም። ፴፰እግዚአብሔር ግን እንደ
ወደደ አገዳን ይሰጠዋል፤ ለእያንዳንዱ ዘርም
አገዳው እየራሱ ነው።
፴፱የፍጥረቱ ሁሉ አካል አንድ አይደለምና፤
የሰው አካል ሌላ ነው፤ የእንስሳም አካል ሌላ
ነው፤ የወፍ አካልም ሌላ ነው፤ የዓሣ አካ
ልም ሌላ ነው። ፵ስማያዊ አካል አለ፤ ምድ
ራዊ አካልም አለ፤ ነገር ግን በሰማይ ያለው
አካል ክብሩ ልዩ ነው፤ በምድርም ያለው
አካል ክብሩ ልዩ ነው። ፵፩የፀሐይ ክብሩ ሌላ
ነው፤ የጨረቃም ክብሩ ሌላ ነው፤ የከዋክብ
ትም ክብራቸው ሌላ ነው፤ ኮከብ ከኮከብ በክ
ብር ይበልጣልና።
፵፪የሙታን ትንሣኤያቸው እንዲሁ ነው፥
በሚፈርስ አካል ይዘራል፤ በማይፈርስ አካል
ይነሣል። ፵፫በውርደት ይዘራል፤ በክብር ይነ
ሣል፤ በድካም ይዘራል፤ በኀይል ይነሣል።
፵፬ሥጋዊ አካል ይዘራል፤ መንፈሳዊ አካል ይነ
ሣል፤ ሥጋዊ አካል አለና መንፈሳዊ አካል
ደግሞ አለ። ፵፭መጽሐፍ እንዲሁ ብሎአልና
የመጀመሪያው ሰው አዳም በነፍስ ሕያው ሆኖ
ተፈጠረ፤ ሁለተኛው አዳም ግን ሕይወትን
የሚሰጥ መንፈስ ነው። ፵፮ነገር ግን አስቀድሞ
ሥጋዊው፥ ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ፥
መንፈሳዊው መጀመሪያው አይደለም። ፵፯መጀ
መሪያው ሰው ከመሬት የተገኘ መሬታዊ ነው፤
ሁለተኛው ሰው ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ ነው።
፵፰መሬታውያኑ እንደዚያ እንደ መሬታዊው
ናቸው፤ ሰማያውያኑም እንደዚያ እንደ ሰማያ
ዊው ናቸው። ፵፱የመሬታዊውን መልክ እንደ
ለበስን እንዲሁ የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እን
ለብሳለን። ፶ወንድሞቻችን ሆይ፥ ይህን እንነግ
ራችኋለን፦ ሥጋዊና ደማዊ የእግዚአብሔርን
መንግሥት አይወርስም፥ የሚፈርሰው የማይፈ
ርሰውን አይወርስም።
፶፩እነሆ፥ አንድ ምሥጢርን እነግራችኋለሁ፥
ሁላችን የምንሞት አይደለም። ፶፪ነገር ግን የኋለ
ኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን እንደ ዐይን ጥቅሻ
በአንድ ጊዜ እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋል፤
ሙታንም የማይፈርሱ ሁነው ይነሣሉ፤ እኛም
እንለወጣለን። ፶፫ይህ የሚፈርሰው የማይፈርስ
ውን፥ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ይለ
ብስ ዘንድ አለውና። ፶፬ይህ የሚፈርሰው የማይ
ፈርሰውን በለበስ ጊዜ፥ የሚሞተውም የማይሞ
ተውን በለበስ ጊዜ፤ “ሞት በመሸነፍ ተዋጠ”
ተብሎ የተጻፈው ያንጊዜ ይፈጸማል። ፶፭“ሞት
ሆይ፥ እንግዲህ መውጊያህ ወዴት አለ? መቃ
ብር ሆይ፥ አሸናፊነትህ ወዴት አለ?” ፶፮የሞት
መውጊያ ኀጢአት ናት፥ የኀጢአትም ኀይልዋ
ኦሪት ናት። ፶፯በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ድል መንሣትን ለሰጠን ለእግዚአብሔር ምስ
ጋና ይሁን። ፶፰እሁንም የተወደዳችሁ ወንድ
ሞቻችን ሆይ፥ የጸናችሁና የማትናወጡ ሁኑ፤
ዘወትር በጎ ምግባርን እብዝታችሁ ለእግዚእብ
ሔር አበርክቱ፤ ስለ ጌታችን መድከማችሁ ለከ
ንቱ እንዳይደለ ታውቃላችሁና።

## ምዕራፍ ፲፮

### ለኢየሩሳሌም ምእመናን ስለሚደረግ እስተዋፅኦ

፩ለቅዱሳን ስለሚደረገው አስተዋፅኦ በገላ
ትያ ላሉት ምእመናን እንደ ደነገግሁት እናን
ተም እንዲሁ እድርጉ። ፪እኔ ስመጣ ይህ የገ
ንዘብ ማዋጣት ያንጊዜ እንዳይሆን፥ ከእናንተ
ሰው ሁሉ በየሳምንቱ እሑድ የተቻለውን ያወ
ጣጣ፤ ያገኘውንም በቤቱ ይጠብቅ። ፫በመጣሁ
ጊዜም ስጦታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ
ዘንድ የመረጣችኋቸውን ሰዎች መልእክቴን
ጨምሬ እልካቸዋለሁ። ፬ለመሄድ ቢቻለኝ ግን
እኔ ራሴ እሄዳለሁና፥ እነርሱም አብረውኝ ይሄ
ዳሉ። ፭መቄዶንያም ደርሼ ወደ እናንተ እመጣ
ለሁ፤ በመቄዶንያ በኩል አልፋለሁና። ፮እናን
ተም ወደምሄድበት ትሸኙኝ ዘንድ ምንእልባት
የሆነውን ቀን ያህል በእናንተ ዘንድ እቈይ፥
ወይም እከርም ይሆናል። ፯እሁን እግረ መንገ
ዴን ላያችሁ እልሻም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር
የፈቀደ እንደ ሆነ የሆነውን ቀን ያህል በእናንተ
ዘንድ እንደምቈይ ተስፋ እደርጋለሁ። ፰እስከ
በዓለ ኀምሳ በኤፌሶን እቈያለሁ። ፱ሥራ የሞላ

፲፭፥፵፭ ዘፍ. ፪፥፯። ፲፭፥፶፩-፶፪ ፩ተሰ. ፬፥፲፭-፲፯። ፲፭፥፶፬ ኢሳ. ፳፭፥፰። ፲፭፥፶፭ ሆሴዕ ፲፫፥፲፬።
፲፮፥፩ ሮም ፲፭፥፳፭-፳፯። ፲፮፥፭ ሐ.ሥ. ፲፱፥፳፩። ፲፮፥፰ ዘሌ. ፳፫፥፲፭-፳፩፤ ዘዳ. ፲፮፥፱-፲፩። ፲፮፥፰-፱ ሐ.
ሥ. ፲፱፥፰-፲።

በት ታላቅ በር ተከፍቶልኛልና፤ ነገር ግን ብዙ
ዎች ተቃዋሚዎች አሉ።
፲ጢሞቴዎስም በመጣ ጊዜ በእናንተ ዘንድ
ያለ ፍርሀት እንዲኖር ተጠንቀቁ፤ እንደ እኔ የእ
ግዚአብሔርን ሥራ ይሠራልና። ፲፩የሚንቀውም
አይኑር፤ ከወንድሞቻችን ጋር እጠብቀዋለሁና፥
ወደ እኔ እንዲመጣ በሰላም ሸኙት።
፲፪ስለ ወንድማችን ስለ አጵሎስም ከወንድ
ሞች ጋር ወደ እናንተ እንዲመጣ መላልሼ
ማልጄው ነበር፤ አሁን ሊመጣ አልወደደም፤
በተቻለው ጊዜ ግን ይመጣል። ፲፫ትጉ፤ በሃይ
ማኖትም ቁሙ፤ ታገሡ፩ ጽኑ፤ ፲፬ሁሉን በፍ
ቅር አድርጉ። ፲፭ወንድሞቻችን ሆይ፥ የእስ
ጢፋኖስና የፈርዶናጥስ፥ የአካይቆስም፪ ቤተ
ሰቦች፥ የአካይያ መጀመሪያዎች እንደ ሆኑ፥
ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደ ሰጡ
ታውቁ ዘንድ እማልዳችኋለሁ። ፲፮እናንተም
እንደ እነዚህ ላሉትና ከእኛ ጋር በሥራ ተባ
ብሮ ለሚደክም ሁሉ ትታዘዙላቸው ዘንድ
እማልዳችኋለሁ። ፲፯እስጢፋኖስ፥ ፈርዶናጥ
ስና አካይቆስም በመምጣታቸው ደስ ይለኛል፤
እናንተ ያጐደላችሁትን እነርሱ ፈጽመዋልና።
፲፰እነርሱ መንፈሴንና መንፈሳችሁን ደስ አሰኝ
ተዋል፤ እንዲህ ያሉትንም ዕወቋቸው።
፲፱በእስያ ያሉ ምእመናን ሰላምታ ያቀርቡ
ላችኋል፤ አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ከእነ
ርሱ ጋር ያሉ ምእመናንም ሁሉ በጌታችን
እጅግ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ፳ወንድሞቻ
ችሁ ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፤ በተቀ
ደሰች ሰላምታ እርስ በርሳችሁ ሰላም ተባ
ባሉ።
፳፩እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በእጄ ጻፍሁ።
፳፪ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው
የተለየ ይሁን፤ ጌታችን ይመጣል። ፳፫የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋራ ይሁን።
፳፬የእኔም ፍቅር በኢየሱስ ክርስቶስ ከእናንተ
ጋር ይሁን። አሜን።

በኤፌሶን ተጽፎ በጢሞቴዎስና በእስጢፋኖስ፥ በፈርዶናጥስና በአካይቆስ እጅ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው መጀመሪያዉ መልእክት ተፈጸመ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ ግሪኩ "ጐልምሱ" ይላል።

፪ "የፈርዶናጥስና የአካይቆስም ቤተሰቦች" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፮፥፲ ፩ቆሮ. ፬፥፲፯። ፲፮፥፲፭ ፩ቆሮ. ፩፥፲፮። ፲፮፥፲፱ ሐ.ሥ. ፲፰፥፪።

# ሁለተኛው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ
# መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

## ምዕራፍ ፩

### ሰላምታና ምስጋና

፩በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ከሆነ ከጳውሎስና ከወንድማችን ጢሞ
ቴዎስ በቆሮንቶስ ሀገር ላለችው የእግዚአሔር
ቤተ ክርስቲያንና በአካይያ ሀገር ላሉ ቅዱሳን
ሁሉ፥ ፪ከእባታችን ከእግዚአብሔርና ከጌታ
ችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ጸጋ ለእናንተ
ይሁን።

፫የምሕረት እባት፥ የመጽናናትም ሁሉ አም
ላክ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚ
እብሔር ይመስገን። ፬እግዚአብሔር በእጽናናን
በዚያ መጽናናት በመከራ ያሉትን ሁሉ ማጽ
ናናት እንችል ዘንድ ከመከራችን ሁሉ ያጽና
ናን እርሱ ይመስገን። ፭የክርስቶስ መከራ በእኛ
ላይ እንደ በዛ መጠን እንዲሁ መጽናናታችንም
በክርስቶስ ይበዛልና። ፮መከራ ብንቀበልም እና
ንተ እንድትድኑና እንድትጽናኑ ነው፤ ብንጽና
ናም እኛ የተቀበልነውን ያን መከራ በመታገሥ
ስለሚደረግ መጽናናታችሁ ነው። ፯ስለ እናንተ
ያለን ተስፋም የጸና ነው፤ መከራችንን እንደ
ተካፈላችሁ መጠን፥ እንዲሁ በመጽናናታችንም
እንደምትተባበሩ እናውቃለን።

፰ወንድሞቻችን ሆይ፥ በእስያ መከራ እንደ
ተቀበልን ልታውቁ እወዳለሁ፤ ለሕይወታችን
ተስፋ እስከንቈርጥ ድረስ ከዐቅማችን በላይ
እጅግ መከራ ጸንቶብን ነበርና። ፱ሙታንን
በሚያስነሣቸው በእግዚአብሔር እንጂ በራሳ
ችን እንዳንታመን በውስጣችን ለመሞት ቈር
ጠን ነበር። ፲እርሱም እንዲህ ካለ ሞት እዳነን፤
ያድነንማል፤ አሁንም እንደሚያድነን እርሱን
እንታመናለን። ፲፩በብዙዎች ጸሎት ጸጋን እና
ገኝ ዘንድ፥ ብዙዎችም በእኛ ፋንታ ያመሰግኑ
ዘንድ እናንተ በጸሎታችሁ ርዱን።

፲፪በእግዚአብሔር ቅርነትና ይቅርታ መመ
ኪያችንና የነጻነታችን ምስክር ይህቺ ናትና፥
በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጸጋ
በዚህ ዓለም፥ ይልቁንም በእናንተ ዘንድ ተመ
ላለስን። ፲፫የምታነቡትንና የምታውቁትን ነው
እንጂ፥ ሌላ የምንጽፍላችሁ የለምና፥ ይህንም
እስከ ፍጻሜ እንደምታስተውሉት ተስፋ አደ
ርጋለሁ። ፲፬እኛ መመኪያችሁ እንደሆን፥ እን
ዲሁ እናንተም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ቀን መመኪያችን እንድትሆኑ በከፊል እንዳወ
ቃችሁ ተስፋ እናደርጋለን።

፲፭በዚህም ታምኜ ጸጋን በዕጥፍ እንድታገኙ
በመጀመሪያ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ መከርሁ።
፲፮በእናንተም በኩል ወደ መቄዶንያ እንዳልፍ፥
ዳግመኛም ከመቄዶንያ እንድመለስና እናንተም
ደግሞ ወደ ይሁዳ ሀገር ትሸኙኝ ዘንድ መከ
ርሁ። ፲፯እንግዲህ ይህን የመከርሁ በውኑ የሠ
ራሁት እንደ አላዋቂ ሰው ሆኜ ነውን? ወይስ
በእኔ በኩል አዎን አዎን፥ አይደለም አይደለም
ማለት እንዲሆን ያን የምመክረው ለሰው ይምሰል
ነውን? ፲፰እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ለእናን
ተም የሚነገረው ቃላችን እውነትና ሐሰት አልተ
ቀላቀለበትም። ፲፱እኛ ማለት እኔ ጳውሎስ፥ ስል
ዋኖስና ጢሞቴዎስ የሰበክንላችሁ የእግዚአብሔር
ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነትና ሐሰት አይደ
ለም፤ ነገር ግን ስለ እርሱ ያስተማርነው እውነት
ነው። ፳እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ሁሉ በክር
ስቶስ እውነት ሆኖአልና፤ ስለዚህም በእርሱ ለእ
ግዚአብሔር ክብር አሜን እንላለን። ፳፩ከእናንተ
ጋር በክርስቶስ ስም የሚያጸናንና የቀባን እግዚ
አብሔር ነው። ፳፪ደግሞም ያተመንና የመንፈስ
ቅዱስን ፈለማ በልቡናችን የሰጠን እርሱ ነው።

---

፩፥፩ ሐ.ሥ. ፲፰፥፩። ፩፥፰ ፩ቆሮ. ፲፭፥፴፪። ፩፥፲፮ ሐ.ሥ.፲፱፥፳፩። ፩፥፲፱ ሐ.ሥ. ፲፰፥፭።

፳፫እኔ ለእናንተ በመራራት ወደ ቆሮንቶስ እን
ዳልመጣሁ፥ ስለ ራሴ እግዚእብሔርን ምስክር
አደርገዋለሁ። ፳፬ደስ የሚላችሁን እንድታደርጉ
እንረዳችኋለን እንጂ እንድታምኑ ግድ የምንላ
ችሁ አይደለም፤ በእምነት ቆማችኋልና።

## ምዕራፍ ፪

፩እንግዲህ እያዘንሁ ወደ እናንተ እንዳልመጣ
በልቤ ይህን ወሰንሁ። ፪እኔ ካሳዘንኋችሁማ እኔ
ካሳዘንሁት በቀር ማን ደስ ያሰኘኛል? ፫የእኔ
ደስታ የሁላችሁ እንደ ሆነ በሁላችሁ እምኜለ
ሁና በመጣሁ ጊዜ ደስ ሊያሰኙኝ ከሚገባቸው
ኀዘን እንዳያገኘኝ ይህን ጻፍሁላችሁ። ፬ከብዙ
መከራና ከልብ ጭንቀት የተነሣ በብዙ እንባ
ይህን ጽፌላችኋለሁ፤ ነገር ግን እጅግ እንደም
ወዳችሁ እንድታውቁ ነው እንጂ እንድታዝኑ
አይደለም።
፭ማንም ያሳዘነኝ ቢሆን፥ እኔን ብቻ ያሳዘነ
አይደለም። ከእናንተ አንድ ሳይቀር ሁላችሁ
ንም አሳዘነ እንጂ፤ እሁንም ሥርዐት እላጸናባ
ችሁም። ፮እንደዚህ ላለው ሰው ከእናንተ ከብ
ዙዎች ያገኘችው ይህች ተግሣጽ ትበቃዋለች።
፯ደግሞም እንዲህ ያለው ሰው ከኀዘን ብዛት
የተነሣ እንዳይዋጥ ይቅር ልትሉትና ልታጽና
ኑት ይገባል። ፰ስለዚህም ከእርሱ ጋር ፍቅርን
እንድታጸኑ እማልዳችኋለሁ። ፱ስለዚህም በሁሉ
ትታዘዙኝ እንደ ሆነ፥ ፈቃዳችሁን ዐውቅ ዘንድ
ጻፍሁላችሁ። ፲ይቅር የምትሉት ቢኖር፥ እኔም
ከእናንተ ጋር ይቅር እለዋለሁ፤ እኔም ይቅር
ያልሁትን በክርስቶስ ፊት ስለ እናንተ ይቅር
ብያለሁ። ፲፩ሰይጣን እንዳያታልለን እሳቡን የም
ንስተው አይደለምና።

### ስለ እግዚአብሔር መንገድ

፲፪ለክርስቶስም ወንጌል ጢሮአዳ በደረስሁ
ጊዜ በእግዚአብሔር በሩ ተከፈተልኝ። ፲፫ወንድ
ሜን ቲቶን ስላላገኘሁት ለሰውነቴ ዕረፍት አላ
ገኘሁም፤ ነገር ግን ከእርሱ ተለይቼ ወደ መቄ
ዶንያ ሄድሁ።

### በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድል ስለ መንሣት

፲፬በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘወትር ድል
በመንሣቱ የሚጠብቀን፥ በየሀገሩም ሁሉ የዕ
ውቀቱን መዓዛ በእኛ የሚገልጥ እግዚእብሔር
ይመስገን። ፲፭በሚድኑትና በሚጠፉት ዘንድ
ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ እኛ ነንና።
፲፮የሞት መዓዛ የሚገባቸው ለሞት፥ የሕይወት
መዓዛ የሚገባቸውም ለሕይወት ናቸው፤ ነገር
ግን ይህ የሚገባው ማን ነው? ፲፯የእግዚእብሔ
ርን ቃል በሌላ ቀላቅለው እንደሚሸቅጡ እንደ
ብዙዎች አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚ
እብሔር እንደ ተላክ በእግዚአብሔር ፊት በክ
ርስቶስ እንናገራለን።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ ደቀ መዛሙርት

፩ወንድሞቻችን፥ አሁን ደግሞ ራሳችንን እያ
መሰገን ልንነግራችሁ እንጀምራለንን? ወይስ
እንደ ሌሎች ስለ እኛ ወደ እናንተ ደብዳቤ እን
ዲጽፉላችሁ፥ ወይስ እናንተ ትጽፉልን ዘንድ
የምንሻው አለን? ፪የእኛስ መጽሐፋችን እናንተ
ናችሁ፤ በልባችን ውስጥም ተጽፋችኋል፤ ትታ
ወቃላችሁም፤ ሰውም ሁሉ ያነብባችኋል። ፫እና
ንተ ራሳችሁም በእኛ የተላከች የክርስቶስ መል
እክት እንደ ሆናችሁ ያውቃሉ፤ ይህቺውም
የተጻፈች በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ነው
እንጂ በቀለም አይደለም፤ በሥጋ ልብ ሰሌዳነት
ነው እንጂ በድንጋይ ሰሌዳም አይደለም።
፬ነገር ግን በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር
ዘንድ እንዲህ ያለ እምነት አለን። ፭ኀይላችን
ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ ከእኛ ከራሳችን እንደ
ሆነ አድርገን ምንም ልናስብ አይገባንም።
፮በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ
ሕግ አገልጋዮች አደረገን፤ ፊደል ይገድላል፥
መንፈስ ግን ሕያው ያደርጋል።

### ስለ መልእክታት መበላለጥ

፯ስለዚያ ስለ አለፈው የፊቱ ብርሃን የእስራ
ኤል ልጆች የሙሴን ፊት መመልከት እስኪሳና
ቸው ድረስ በዚያች በድንጋይ ላይ በፊደል ስተ
ቀረጸች ለሞት መልእክት ክብር ከተደረገላት፥
፰ለመንፈስ ቅዱስ መልእክትማ ምንኛ እጅግ
ክብር ሊደረግ ይገባ ይሆን? ፱ኵነኔን ለምታ
መጣ መልእክት ብዙ ክብር ከተደረገላት የጽ
ድቅ መልእክትማ ምን ያህል ትከብርና ትመ
ሰገን ይሆን? ፲በዚህ ፍጹም ክብር ባነጻጸሯት
ጊዜ የከበረችው እንዳልከበረች ትሆናለችና።

፪፥፲፪-፲፫ ሐ.ሥ. ፳፥፩። ፫፥፫ ዘፀ. ፳፬፥፲፪፤ ኤር. ፴፩፥፴፫፤ ሕዝ. ፲፩፥፲፱፤ ፴፮፥፳፮። ፫፥፮ ኤር. ፴፩፥፴፩።
፫፥፯ ዘፀ. ፴፬፥፳፱።

፲፩ያ የሚያልፈው ክብር ካገኘ፥ ያ ጸንቶ የሚኖ
ረውማ እንዴት እጅግ ክብር ያገኝ ይሆን?
፲፪እንግዲህ ይህን ያህል ተስፋ ካለን በግልጥ ፊት
ለፊት ልንቀርብ እንችላለን። ፲፫የዚያን ይሻር የነበ
ረውን መጨረሻ፥ የእስራኤል ልጆች እንዳያዩት
ፊቱን ይሸፍን እንደ ነበረው እንደ ሙሴ አይደለም።
፲፬ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ ልባቸው ተሸፍኖአል፤
ያም መጋረጃ ብሉይ ኪዳን በተነበበት ዘመን ሁሉ
ጸንቶ ኖሮአል፤ ክርስቶስ እስኪያሳልፈው ድረስ አል
ተገለጠምና። ፲፭እስከ ዛሬም የሙሴን ሕግ ሲያነበቡ
ያ መጋረጃ ልባቸውን ይሸፍናቸዋል። ፲፮ወደ እግዚ
አብሔር በተመለሱ ጊዜ ግን ያ መጋረጃ ከእነርሱ
ይርቃል። ፲፯እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፥ የእግዚአ
ብሔር መንፈስ ባለበትም በዚያ ነጻነት አለ። ፲፰እኛስ
ሁላችን ፊታችንን ገልጠን በመስተዋት እንደሚያይ
የእግዚአብሔርን ክብር እናያለን፤ ከእግዚአብሔር
መንፈስ እንደ ተሰጠን መጠን የእርሱን አርአያ እን
መስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንገባለን።፭

## ምዕራፍ ፬

### ስለ ሐዋርያዊ አገልግሎት

፩ስለዚህ እንደ ቸርነቱ የሰጠን ይህ መልእክት አለ
ንና አንሰለችም። ፪ነገር ግን በስውር የሚሠራውን
አሳፋሪ ሥራ እንተወው፤ በተንኰልም አንመላለስ፤
የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅል፤ ለሰ
ውም ሁሉ አርአያ ስለ መሆን እውነትን ገልጠን
በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን እናጽና። ፫ወንጌላ
ችን የተሰወረ ቢሆንም እንኳ፥ የተሰወረባቸው ለሚ
ጠፉት ነው። ፬እግዚአብሔርን የሚመስለው የክርስ
ቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ
ዓለም አምላክ፮ ልባቸውን አሳውሮአልና። ፭ኢየሱስ
ክርስቶስን ጌታ እንደ ሆነ እንሰብካለን እንጂ ራሳ
ችንን የምንሰብክ አይደለም፤ ስለ ኢየሱስ ክርስቶ
ስም ብለን ራሳችንን ለእናንተ አስገዛን። ፮በጨለማ
ውስጥ "ብርሃን ይብራ" ያለ እግዚአብሔር በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ፊት የክብሩን ዕውቀት ብርሃን በልባ
ችን አብርቶልናልና።

### በሸክላ ዕቃ ውስጥ ስላለው መዝገብ

፯ነገር ግን ከእኛ ያይደለ ከእግዚአብሔር የተ
ገኘ ታላቅ ኀይል ይሆን ዘንድ በሸክላ ዕቃ
ውስጥ ይህ መዝገብ አለን። ፰በሁሉ መከራን
እንቀበላለን፤ ነገር ግን አንጨነቅም፤ እንናቃ
ለን፥ ነገር ግን ተስፋ አንቈርጥም። ፱እንሰደዳ
ለን፤ ነገር ግን አንጣልም፤ እንወድቃለን፤ ነገር
ግን አንጠፋም። ፲የክርስቶስ ሕይወቱ በዚህ
በሟች ሰውነታችን ላይ ይገለጥ ዘንድ፥ ዘወ
ትር የክርስቶስን ሞት በሥጋችን እንሸከማለን።
፲፩በሕይወት የምንኖር እኛም በሟች ሰውነታችን
ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱ ይገለጥ ዘንድ፥
ዘወትር ስለ ኢየሱስ ክስርቶስ ብለን ተላል
ፈን ለሞት እንሰጣለን። ፲፪ስለዚህም ሞት በእኛ
ላይ፥ ሕይወትም በእናንተ ላይ ይሠራል።፯
፲፫አንድ የእምነት መንፈስ አለን፤ መጽሐፍ፥
"አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ" እንዳለ እኛም
አመን፤ ስለዚህም ተናገርን። ፲፬ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስን ያስነሣው እርሱ እኛንም እንደ እርሱ
እንዲያስነሣን፥ ከእናንተም ጋር በፊቱ እንዲያቆ
መን እናውቃለን። ፲፭ጸጋው በብዙዎች ላይ ትት
ረፈረፍ ዘንድ፥ የእግዚአብሔርም የክብሩ ምስ
ጋና ይበዛ ዘንድ ሁሉ ስለ እናንተ ነውና።

### ስለ ውሳጣዊና አፍአዊ ሰውነት

፲፮ስለዚህ አንሰልች፤ በውጭ ያለው ሰውነ
ታችን ያረጃልና፤ በውስጥ ያለው ሰውነታችን
ግን ዘወትር ይታደሳል። ፲፯ቀላል የሆነው የጊ
ዜው መከራችን ክብርንና ጌትነትን ለዘለዓለም
አብዝቶ ያደርግልናልና። ፲፰የማይታየውን እንጂ
የሚታየውን ተስፋ አናደርግም፤ የሚታየው
ኀላፊ ነውና፥ የማይታየው ግን ለዘለዓለም የሚ
ኖር ነው።

## ምዕራፍ ፭

### ስለ ምድራዊና ሰማያዊ ቤት

፩በምድር ያለው ማደሪያ ቤታችን ቢፈርስም፥
በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ የሰው እጅ ያል
ሠራው ዘለዓለማዊ ቤት እንዳለን እናውቃለን።
፪ስለ እርሱ የምንደክምለትን በሰማይ ያለውን
ቤታችንን እንለብስ ዘንድ እርሱን ተስፋ እና
ደርጋለን። ፫ከለበስነውም በኋላ ዕራቁታችንን
የምንገኝ አይደለንም። ፬በዚህ ቤት ውስጥ ሳለ
ንም ከከባድነቱ የተነሣ እጅግ እናዝናለን፤ ነገር

---

፭ ግሪኩ "ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን" ይላል።
፮ ግእዙ "...እግዚእብሔር እምላክ ዘለዓለም" ይላል።
፯ ግእዙ "ይእዜሰ ጸንዐ ላዕሌነ ሞት እንዘ ሕይወት ኀቤነ" ይላል።

፫፥፲፫ ዘፀ. ፴፬፥፴፫። ፫፥፲፮ ዘፀ. ፴፬፥፴፬። ፬፥፮ ዘፍ. ፩፥፫። ፬፥፲፫ መዝ. ፻፲፭፥፲።

ግን ሟች በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ሌላ ልንለ
ብስ እንጂ ልንገፈፍ እንወድም። ፭ለዚህም ያዘ
ጋጀን እግዚአብሔር ነው፤ እርሱም የመንፈስ
ቅዱስን ፈለማ ሰጠን።

፮እንግዲህ ሁልጊዜ እመኑ፥ ጨክኑም፤ በዚህ
ሥጋ ሳላችሁም እናንተ እንግዶች እንደ ሆናችሁ
ታውቃላችሁ፤ ከሥጋችሁም ተለይታችሁ ወደ
ጌታችን ትሄዳላችሁ።[፩] ፯በእምነት እንኖራለን፤
በማየትም አይደለም። ፰ታምነናል፤ ይልቁንም
ከሥጋችን ተለይተን ወደ ጌታችን እንሄዳለንና
ደስ ይለናል። ፱አሁንም ብንኖርም፥ ብንሞትም
እርሱን ደስ ለማሰኘት እንጥራለን። ፲መልካም
ቢሆን፥ ክፉም ቢሆን በሥጋችን እንደ ሠራነው
ዋጋችንን እንቀበል ዘንድ፥ ሁላችን በክርስቶስ
የፍርድ ዙፋን ፊት እንቆማለንና።

## ስለ መምህራን

፲፩እግዚአብሔርን መፍራት ዐውቀን ሰዎችን
እናሳምናለን፤ ለእግዚአብሔር ግን እኛ የተገ
ለጥን ነን፤ እንዲሁም በልቡናችሁ የተገለጥን
እንደ ሆን እንታመናለን። ፲፪በዚህ ደግሞ በእና
ንተ ዘንድ ራሳችንን የምናመሰግን አይደለም፤
ነገር ግን እኛ እንደምንመካባችሁ፥ እናንተም
በእኛ እንድትመኩ፥ ከልብ ሳይሆን ለሰው ይም
ሰል በሚመኩ ሰዎች ዘንድ መልስ እንዲሆናችሁ
ምክንያትን እንሰጣችኋለን። ፲፫እኛ ሰነፎች ብን
ሆንም፥ ስንፍናችን ለእግዚአብሔር ነው፤ ዐዋ
ቂዎች ብንሆንም ዐዋቂነታችን ለእናንተ ነው።
፲፬የክርስቶስ ፍቅር በዚህ አሳብ እንድንጸና ያስ
ገድደናል፤ ሁሉ ፈጽመው ስለ ሞቱ አንዱ ስለ
ሁሉ ቤዛ ሆኖ ሞቶአልና። ፲፭በሕይወት የሚኖ
ሩትም ስለ እነርሱ ቤዛ ሆኖ ለሞተውና ለተነሣ
ውም እንጂ ወደፊት ለራሳቸው የሚኖሩ እንዳይ
ሆኑ እርሱ ስለ ሁሉ ቤዛ ሆኖ ሞተ።

፲፮ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ በሥጋ የምናውቀው
የለም፤ ክርስቶስንም በሥጋ ብናውቀው አሁን
ግን ከእንግዲህ ወዲህ የምናውቀው አይደለም።
፲፯አሁንም በክርስቶስ የሆነው ሁሉ አዲስ ፍጥ
ረት ነው፤ የቀደመውም አለፈ፤ እነሆ ሁሉም
አዲስ ሆነ።

## ስለ ማስታረቅ መልእክት

፲፰ነገር ግን ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ከእ
ስታረቀን፥ የማስታረቅ መልእክትንም ከሰጠን
ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ፲፱ኀጢአታቸውን
ይቅር ብሎ በደላቸውንም ሳያስብ እግዚአብ
ሔር በክርስቶስ ዓለሙን ከራሱ ጋር አስታር
ቆአልና፤ የዕርቅ ቃሉንም በእኛ ላይ አደረገ፤
የይቅርታውንም መልእክት ሰጠን። ፳እኛስ በክ
ርስቶስ እምሳል እንለምናለን፤ እግዚአብሔርም
በእኛ መጽናናትን ይሰጣችኋል፤ ከእግዚአብሔ
ርም ጋር ትታረቁ ዘንድ በክርስቶስ እንለምና
ችኋለን። ፳፩ኀጢአት የሌለበት እርሱ እኛን ለእ
ግዚአብሔር ያጸድቀን ዘንድ ስለ እኛ ራሱን
እንደ ኃጥእ አድርጓልና።[፪]

## ምዕራፍ ፮

### ምግባርን ስለ ማቅናት

፩ከእርሱም ጋር አብረን እየሠራን፥ የተቀ
በላችኋትን የእግዚአብሔር ጸጋ ለከንቱ እን
ዳታደርጓት እንማልዳችኋለን። ፪እንዲህ ብሎ
አልና፥ "በተመረጠችው ቀን ሰማሁህ፤ በመ
ዳንም ቀን ረዳሁህ" እነሆ፥ የተመረጠችው
ቀን ዛሬ ናት። ፫አገልግሎታችንም እንዳይነ
ቀፍ፥ በአንዳች ነገር ማሰናከያ እንዳንሰጥ
እንጠንቀቅ። ፬ነገር ግን በሁሉ ራሳችንን እቅ
ንተን፥ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንሁን፤
በብዙ ትዕግሥትና በመከራ፥ በችግርና በጭ
ንቀት ሁሉ፥ ፭በመገረፍና በመታሰር፥ በድ
ካምና በመታወክ፥ በመትጋትና በመጾም፥
፮በንጽሕናና በዕውቀት፥ በምክርና[፩] በመታ
ገሥ፥ በቸርነትና በመንፈስ ቅዱስ፥ አድ
ልዎ በሌለበት ፍቅር፥ ፯በእውነት ቃል፥
በእግዚአብሔር ኀይል ለቀኝና ለግራ በሚ
ሆን የጽድቅ የጦር ዕቃ፥ ፰በክብርና በው
ርደት፥ በምርቃትና በርግማን፥ እንደ አሳ
ቾች ስንታይ እውነተኞች ነን። ፱እንደማይታ
ወቁ ስንታይ የታወቅን ነን፤ እንደ ሰነፎች
ስንታይም ልባሞች ነን፤[፪] እንደ ሙታን ስን

---

፩ ግሪኩ "እኛ ሁልጊዜ እናምናለን በሥጋም ሳለን ከጌታ እንድንርቅ እናውቃለን" ይላል።

፪ ግሪኩ "እኛ በእርሱ ሁነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኀጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኀጢአት አደ
ረገው" ይላል።

፩ "በምክር" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ "እንደ ሰነፎች ስንታይም ልባሞች ነን" የሚለው በግሪኩ የለም።

፭፥፲ ሮሜ ፲፬፥፲። ፮፥፪ ኢሳ. ፵፱፥፰። ፮፥፭ ሐ.ሥ. ፲፮፥፳፫።

ታይ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ስንሆንም አን
ገደልም። ፲ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ
ተኞች ነን፤ እንደ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን
እናበለጽጋለን፤ ምንም የሌለን ስንሆን ሁሉ
በእጃችን ነው።

### ስለ ቆሮንቶስ ሰዎች

፲፩የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፥ ለእናንተ አፋ
ችን የተከፈተ ነው፤ ልባችንም የሰፋ ነው።
፲፪ከእናንተ የደረሰ ኀዘን በእኛ የለም፤ ከእ
ኛም በእናንተ ላይ የደረሰ ኀዘን የለም፤ ነገር
ግን በልባችሁ አዝናችኋል። ፲፫ልጆቼ እንደ
መሆናችሁ፥ ይህን እላችኋለሁ፤ ከእናንተ
ላይ ስለሚገባኝ ብድራቴ እናንተ ፍቅራች
ሁን አስፉልኝ።

### ከማያምኑ ስለ መለየት

፲፬ተጠራጣሪዎች አትሁኑ፤[፫] ወደማያምኑ
ሰዎች አንድነትም አትሂዱ፤ ጽድቅን ከኀ
ጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ማን ነው?
ብርሃንንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅል ማን
ነው? ፲፭ክርስቶስን ከቤልሆር ጋር አንድ የሚ
ያደርገው ማን ነው? ወይስ ምእመናንን ከመ
ናፍቃን ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው
ማን ነው? ፲፮የእግዚአብሔርን ታቦትስ[፬] በጣ
ዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? የሕ
ያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደ
ለንምን? እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተና
ገረ፥ "እኔ በእነርሱ አድራለሁ፤ በመካከላ
ቸውም እኖራለሁ፤ አምላካቸውም እሆናቸዋ
ለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል።" ፲፯ስለ
ዚህም "ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ፤
ከእነርሱም ተለዩ፤ ወደ ርኩሳንም አትቅ
ረቡ፥ እኔም እቀበላችኋለሁ። ፲፰አባት እሆና
ችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆች
ትሆኑኛላችሁ አለ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብ
ሔር።"

## ምዕራፍ ፯

### ሰውነትን ስለ ማንጻት

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ እንግዲህ ይህ ተስፋ
ያለን ስለሆን ራሳችንን እናንጻ፤ ሥጋችንን እና
ርክስ፤ ነፍሳችንንም እናሳድፍ፤ እግዚአብሔር
ንም በመፍራት የምንቀደስበትን እንሥራ። ፪እሁ
ንም ወንድሞቻችን ሆይ፥ ታገሡን፥[፭] የበደል
ነው የለም፤ የገፋነውም የለም፤[፮] ያጠፋነውም
የለም፤ የቀማነውም የለም። ፫ይህንም የምለው
በእናንተ ለመፍረድ አይደለም፤[፯] ለሞትም፥
ለሕይወትም ቢሆን እናንተ በልባችን እንዳላ
ችሁ ፈጽሜ ተናግሬአለሁና። ፬በእናንተ ዘንድ
እንዲሁ ብዙ መወደድ አለኝ፤ ስለ እናንተም
የምመካበት ብዙ ነው፤ መጽናናትንም አገኘሁ፤
ከመከራዬም[፰] ሁሉ ይልቅ ደስታዬ በዛልኝ።
፭ወደ መቄዶንያም በደረስን ጊዜ ለሰውነታ
ችን ጥቂት ስንኳን ዕረፍት አላገኘንም፤ በሁ
ሉም መከራ አጸኑብን እንጂ፤ በውጭም መጋ
ደል ነበር፤ በውስጥም ፍርሀት ነበር። ፮ነገር
ግን ያዘኑትን የሚያጽናና እርሱ እግዚአብሔር
በቲቶ መምጣት አጽናናን። ፯በመምጣቱ ብቻ
አይደለም፤ በአጽናናችሁት ማጽናናትም ነው
እንጂ፤ ለእኛ እንደምታስቡና እንደምትቀኑ ፍቅ
ራችሁን ነግሮናል፤ ይህንም ሰምቼ ደስታዬ
በእናንተ በዛ።

### ስለሚገባ ኀዘን

፰መጀመሪያ በጻፍሁት መልእክት ባሳዝናች
ሁም እንኳ አያጸጽተኝም፤ ብጸጸትም፥ እነሆ
ያች መልእክት ለጥቂት ጊዜ ብቻ እንዳሳዘነቻ
ችሁ አያለሁ። ፱አሁን ግን እኔ ስለ እርሷ በብዙ
ደስ ይለኛል፤ ደስታዬም ስለ አዘናችሁ አይደ
ለም፤ ንስሓ ልትገቡ ስለ አዘናችሁ እንጂ፤ ከእ
ናንተ አንዱ ስንኳ እንዳይጠፋ፥ ስለ እግዚአብ
ሔር ብላችሁ አዝናችኋልና። ፲ስለ እግዚአብሔር

---

፫ "ተጠራጣሪዎች አትሁኑ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፬ ግሪኩ "የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር አንድ የሚያደርግ ማን ነው" ይላል።

፭ ግሪኩ "ልባችሁን አስፉልን" ይላል።

፮ "የገፋነውም የለም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፯ ግእዙ "ለአድልዎ" ይላል።

፰ ግሪኩ "በመከራችን ሁሉ ደስታዬ በዛልኝ" ይላል።

፮፥፲፮ ዘሌ. ፳፮፥፲፪፤ ሕዝ. ፴፯፥፳፯፤ ፩ቆሮ. ፫፥፲፮፤ ፮፥፲፱። ፮፥፲፯ ኢሳ. ፶፪፥፲፩።
፮፥፲፰ ፪ሳሙ. ፯፥፲፬፤ ፩ዜ.መ. ፲፯፥፲፫፤ ኢሳ. ፵፫፥፮፤ ኤር. ፴፩፥፱። ፯፥፭ ፪ቆሮ. ፪፥፲፫።
፯፥፲ ማቴ. ፳፯፥፫፭።

ተብሎ የሚደረግ ኀዘን የዘለዓለም ሕይወትን
የሚያስጥ[፳] ንስሓ ነው። ስለ ዓለም የሚደረግ
ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል። ፲፩ እነሆ፥ ያ ስለ እግ
ዚአብሔር ብላችሁ ያደረጋችሁት ኀዘን ምንም
የማታውቁ እስከ መሆን ደርሳችሁ፥ ራሳችሁን
በበጎ ሥራና በንጽሕና እስክታጸኑ ድረስ፥ ትጋት
ንና ክርክርን፥ ቍጣንና ፍርሀትን፥ ናፍቆትንና
ቅንዐትን፥ በቀልንም አደረገላችሁ፤ ፲፪ ይህን የጻ
ፍሁላችሁ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ እንደ
ተጋችሁ ይታወቅ ዘንድ ነው እንጂ ስለ በደለና
ስለ ተበደለ ሰው አይደለም። ፲፫ ስለዚህም ተጽ
ናንተናል፤ በመጽናናታችንም ስለ ቲቶ ደስታ
አብልጦ ደስ አለን፤ በሁላችሁ ዘንድ ሰውነቱን
አሳርፋችኋታልና። ፲፬ ስለ እናንተ ለእርሱ በተ
መካሁበት ሁሉ አላሳፈራችሁኝምና፤ ነገር ግን
ሁሉን ለእናንተ በእውነት እንደ ተናገርን፥ እን
ደዚሁ ደግሞ በቲቶ ፊት ትምክህታችን እው
ነት ሆነ። ፲፭ [፳፩] ስለዚህም እጅግ ያመሰግናችኋል፤
እንደ ታዘዛችሁለት፥ በመፍራትና በመደንገጥም
እንደ ተቀበላችሁት ያስባችኋል። ፲፮ እኔም በሁሉ
ነገር እተማመናችኋለሁና ደስ ይለኛል።

## ምዕራፍ ፰

### የመቄዶንያ ቤተ ክርስቲያን አስተዋፅኦ

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስ
ቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እን
ግራችኋለሁ። ፪ በብዙ መከራ ከመፈተናቸው
የተነሣ ደስታቸው በዝቶአልና፤ በድህነታቸው
ጥልቅነትም የለጋስነታቸው ባለጠግነት በዝታለ
ችና። ፫ እነርሱ ሲቻላቸው፥ ሳይቻላቸውም እን
ስጥ በማለት ቈራጦች ለመሆናቸው ምስክራ
ቸው እኔ ነኝና። ፬ ለቅዱሳን ስለሚሆነው አገል
ግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት መላልሰው
ማለዱን። ፭ እነርሱ አስቀድመው በፈቃዳቸው፥[፳፪]
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰውነታቸውን ለእ
ግዚአብሔርም፥ ለእኛም አሳልፈው ሰጥተዋ
ልና እኛ እንደ አሰብነው አይደለም፤ ፮ [፳፫] ይህ
ንም የቸርነት ሥራ እንደ ጀመረ ይፈጽምላችሁ
ዘንድ ቲቶን ማለድነው። ፯ በሁሉ ነገር በእምነ
ትና በቃል፥ በዕውቀትም፥ በትጋትም በእናንተ
ዘንድ በሆነው ሁሉ እኛን በመውደዳችሁ ፍጹ
ማን እንደ ሆናችሁ፥ እንዲሁም ደግሞ ይህቺን
ስጦታ አብዙ።

፰ በግድ የምላችሁ አይደለም፤ ነገር ግን ከእ
ናንተ ለዚህ ሥራ የሚተጉለት አሉና የፍቅ
ራችሁን እውነተኛነት አሁን መርምሬ ተረ
ዳሁ። ፱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸርነቱን
ታውቃላችሁ፤ በእርሱ ድህነት እናንተ ባለጸ
ጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ባለጸጋ ሲሆን፥ ስለ
እናንተ ራሱን ድሃ አደረገ። ፲ በዚህም የሚጠ
ቅማችሁን እመክራችኋለሁ፤ ይህን ከማድረጋ
ችሁ በፊት ፈቅዳችኋልና፤ ከአምና ጀምሮም
ይህን ጀምራችኋል። ፲፩ አሁንም አድርጉ፤ ፈጽ
ሙም፤ መፍቀድ ከመሻት ነውና፤ ማድረግም
ከማግኘት ነውና። ፲፪ ፈቃድ ካለም፥ ሰው በሚ
ቻለው መጠን ቢሰጥ ይመሰገናል፤ በማይቻለ
ውም መጠን አይደለም። ፲፫ በዚህ ወራት ተካ
ክላችሁ እንድትኖሩ ነው እንጂ ሌላው እንዲያ
ርፍ እናንተን የምናስጨንቅ አይደለም። ፲፬ ኑሮ
አችሁ በሁሉ የተካከለ ይሆን ዘንድ፥ የእናንተ
ትርፍ የእነርሱን ጕድለት ይመላልና፥ የእነር
ሱም ትርፍ የእናንተን ጕድለት ይመላልና።
፲፭ መጽሐፍ እንዳለ፥ "ብዙ ያለው አላተረፈም፤
ጥቂት ያለውም አላጐደለም።"

### ስለ ቲቶና ጓደኞቹ

፲፮ [፳፬] በቲቶ ልብ ስለ እናንተ ያን መትጋት
የሰጠ እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው። ፲፯ ልመ
ናችንንም[፳፭] ተቀብሎ፥ ጨክኖ ወደ እናንተ
ይመጣ ዘንድ ቸኵሏል። ፲፰ ስለ ወንጌል ትም
ህርት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያመሰገኑትን
ወንድማችንንም ከእርሱ ጋር ልክናል። ፲፱ ይህም
ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን
ክብርና የእኛን በጎ ፈቃድ ለማሳየት በምናገ
ለግልባት በዚች ጸጋ ከእኛ ጋር አንድ ይሆን
ዘንድ በአብያተ ክርስቲያናት ተሾመ። ፳ ስለም
ናገለግለው ስለዚህ ለጋስ ስጦታ ማንም እንዳይ

---

፳ ግሪኩ "ጸጸት የሌለበት ንስሓ ነው" ይላል።

፳፩ ግሪኩ "ፍቅሩ በእናንተ ላይ እጅግ በዝትዋል" ይላል።

፳፪ "በፈቃዳቸው" የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፫ ግእዙ "ወአስተፍሥሐኒ ቲቶ" ይላል።

፳፬ ግእዙ "ዘወሀበነ ለነ ንጽሐቅ... በከመ ይቤ ቲቶ" ይላል።

፳፭ ግእዙ "ሥላጤክሙ" ይላል።

፰፥፩-፬ ሮም ፲፭፥፳፮። ፰፥፲፭ ዘፀ. ፲፮፥፲፰።

ነቅፈን እንጠነቀቃለን። ፳፩በእግዚአብሔር ፊት
ብቻ ያይደለ፥ ነገር ግን በሰው ፊትም መል
ካሙን ነገር እናስባለንና። ፳፪በብዙ የፈተንነው
ንና በሁሉም ነገር ትጉህ ሆኖ ያገኘነውን አሁ
ንም በእናንተ እጅግ ስለሚታመን ከፊት ይልቅ
እጅግ ትጉ የሚሆነውን ወንድማችንን ከእነርሱ
ጋር እንልካለን። ፳፫ቲቶም ቢሆን፥ ስለ እና
ንተ አብሮኝ የሚሠራ ጓደኛዬ ነው፥ ወንድሞ
ቻችንም ቢሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ክብር[፳፫] የአ
ብያተ ክርስቲያናት ሐዋርያት ናቸው። ፳፬አሁ
ንም መዋደዳችሁንና እኛም በእናንተ የምንመ
ካበትን ሥራ በአብያተ ክርስቲያናት ፊት በግ
ልጥ አሳዩአቸው።

## ምዕራፍ ፱

### ስለ ቅዱሳን አገልግሎት

፩ለቅዱሳን ስለሚደረገው አገልግሎት የምጽ
ፍላችሁ ብዙ አለኝ[፩] ፪እናንተ እንደምትተጉ
አውቃለሁና፤ ስለዚህም "የአካይያ ሰዎች እኮ
ከአምና ጀምሮ አዘጋጅተዋል" ብዬ በመቄዶ
ንያ ሰዎች ዘንድ አመሰግንኋችሁ፤ እነሆም የእ
ናንተ መፎካከር ብዙዎችን ሰዎች አትግቶአቸ
ዋል። ፫በዚህም ያመሰገንናችሁ ምስጋና በእነ
ርሱ ዘንድ ሐሰት እንዳይሆንብን፥ እንደ ነገር
ናቸውም ተዘጋጅታችሁ እንዲያገኙአችሁ ወን
ድሞችን ወደ እናንተ ላክናቸው።[፫] ፬ምናልባት
የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር ቢመጡና ሳታዘ
ጋጁ ቢያገኙአችሁ እናንተ ታፍራላችሁ ባል
ልም እኛ ስለ እናንተ ከነገርናቸው የተነሣ እና
ፍራለን። ፭ስለዚህም አስቀድመው ወደ እና
ንተ መጥተው በቅድሚያ የተናገራችኋትን በረ
ከታችሁን እንዲያዘጋጁ ወንድሞችን ማለድሁ፤
እንደዚህም የተዘጋጀ ይሁን፤ በረከትን እንደ
ምታገኙበት እንጂ በንጥቂያ እንደ ተወሰደባ
ችሁ አይሁን።

፮እሳንሶ የሚዘራ ለእርሱ እንዲሁ መከሩ ያን
ስበታል፤ በብዙ የሚዘራ ግን በብዙ ያመር
ታል። ፯ሁሉ ልቡ እንደ ወደደ ያድርግ፤ በደ
ስታ ይስጡ እንጂ በግድ አይሆንም፤ እግዚአ
ብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና። ፰እግ
ዚአብሔር መልካሙን ነገር ሁሉ ሊያበዛላችሁ
ይችላል፤ ፍጹም በረከቱንም ለዘወትር ያበዛላ
ችሁ ዘንድ፥ ለሁሉም ታተርፉታላችሁ፤ በጎ
ሥራ መሥራትንም ታበዛላችሁ። ፱"በተነ፤ ለድ
ሃም ሰጠ፤ ጽድቁም ለዘለዓለም ይኖራል" ብሎ
መጽሐፍ እንደ ተናገረ። ፲እርሱ ዘርን ለዘሪ ይሰ
ጣል፤ እህልንም ለምግብ ይሰጣችኋል፤ ዘራች
ሁንም ያበዛላችኋል፤ የጽድቃችሁንም መከር
ያበጃል። ፲፩ለብዙ ሰዎች ስለ ሰጣችሁም የእ
ግዚአብሔርን ምስጋና በምታደርግላችሁ ልግ
ሰና ሁሉ ባለጸጎች ትሆናላችሁ። ፲፪ይህቺ የዚህ
ሥራ አገልግሎት ግዳጅ የምትፈጽመው ለዚህ
ለቅዱሳን ችግር መሟላት ብቻ አይደለም፤ በቅ
ዱሳን ዘንድም[፲፪] ደግሞ የእግዚአብሔርን ምስ
ጋና ታበዛለች። ፲፫ክርስቶስ ላስተማራት ትም
ህርት ታዝዛችኋልና፥ ሁላችሁም ደስ ብሎአች
ሁና ተባብራችሁ አወጣጥታችኋልና በዚች በሃ
ይማኖታችሁ ፈተና[፲፫] ምክንያት እግዚአብሔርን
ያመሰግኑታል፤ ፲፬እነርሱም ስለ እናንተ ይጸል
ያሉ፤ ስለ አደረባችሁ ታላቅ የእግዚአብሔር
ጸጋም ሊያዩአችሁ ይመኛሉ። ፲፭ስለማትመረ
መርና ባላሰቡአት ጊዜ ስለምትመጣው[፲፭] ጸጋው
እግዚአብሔር ይመስገን።

## ምዕራፍ ፲

### ስለ መንፈሳዊ የጦር ዕቃ

፩ወንድሞቻችን ሆይ፥ እኔ ጳውሎስ በእናንተ
ዘንድ ፊት ለፊት ሳለሁ ትሑት የሆንሁ፥ ከእ
ናንተ ብርቅ ግን የምደፍራችሁ በክርስቶስ የዋ
ህነትና ቸርነት እማልዳችኋለሁ፥ በፍቅራችሁ
እታመናለሁና።[፩] ፪ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ
እሠራለሁ፤ በሥጋዊ ሥርዐትም እንደምንኖር
አድርገው በሚጠረጥሩን ሰዎች ላይ በድፍረት
ለመናገር አስባለሁ፤ እናንተ ግን በዚህ ዓይነት

---

፳፫ ግሪኩ "የክርስቶስ ክብር" ይላል።

፩ ግሪኩ "ልጽፍላችሁ አያስፈልግም" ይላል።

፫ ግሪኩ "ላከኋቸው" ይላል።

፲፪ ግሪኩ "በብዙዎች ዘንድ" ይላል።

፲፫ ግሪኩ "በአገልግሎታችሁ ፈተና" ይላል።

፲፭ "ባላሰቡአት ጊዜም ስለምትመጣው" የሚለው በግሪኩ የለም።

፩ "በፍቅራችሁ እታመናለሁና" የሚለው በግሪኩ የለም።

፰፥፳፩ ምሳ. ፫፥፬። ፱፥፱ መዝ. ፻፲፩፥፱። ፱፥፲ ኢሳ. ፶፭፥፲።

ድፍረት እንድናገር እንዳታደርጉኝ እለምናችኋ
ለሁ። ፫በሥጋችንስ እንሄዳለን፤ ነገር ግን በእ
ርሱው ሥርዐት የምንሄድና የምንዋጋ አይደ
ለም። ፬የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ጽኑ
ምሽግን በሚያፈርስ በእግዚአብሔር ኀይል ነው
እንጂ። ፭ልብ ሁሉ ይማረክ ዘንድ ኀሊናም ለክ
ርስቶስ ይገዛ ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ የሚ
ታበየውንና ከፍ ከፍ የሚለውን እናፈርሳለን።፪
፮እናንተ ትእዛዝን በፈጸማችሁ ጊዜ የማይገዛ
ውን ሁሉ እኛ ልንበቀለው ዝግጁዎች ነን።
፯በፊታችሁ ያለውን ተመልከቱ፤ ማንም በክ
ርስቶስ ያመነ ቢሆን፥ ይህን እንደ ገና በራሱ
ይቍጠረው፤ እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ እኛም
እንዲሁ ነንና። ፰እናንተን ስማነጽ እንጂ፥ እናን
ተን ለማፍረስ ያይደለ፥ እግዚአብሔር በእናንተ
ላይ በሰጠን ሥልጣን እጅግ የተመካሁት መመ
ካት ቢኖር አላፍርም። ፱ነገር ግን በመልእክቶቼ
የማስፈራራችሁ እንዳይመስላችሁ፥ ይህን ትምክ
ሕቴን እተወዋለሁ። ፲ከሰዎች መካከል "መልእ
ክቶቹ ከባዶችና አስጨናቂዎች ናቸው፤ ሰውነቱ
ግን ደካማ ነው፤ ነገሩም ተርታ ነው" የሚሉ
አሉና። ፲፩ነገር ግን ይህን ነገር የሚናገር ይህን
ይወቅ፤ በሌለንበት ጊዜ በመልእክታችን እንደ
ተገለጠው እንደ ቃላችን፥ ባለንበትም ጊዜ በሥ
ራችን እንዲሁ ነን። ፲፪እነርሱ ራሳቸውን በእስ
ቡትና በገመገሙት መጠን ራሳቸውን ከሚያመ
ስግኑት ሰዎች ጋር ራሳችንን ልንቈጥር፥ ወይም
ራሳችንን ልናስተያይ አንደፍርም፤ እነርሱ ራሳ
ቸውም የሚናገሩትን ትርጕሙን አያውቁትም።
፲፫እኛስ ወደ እናንተ እስከንደርስ ድረስ እግዚአ
ብሔር በወሰነልን ሕግና ሥርዐት እንጂ፥ ከዐቅ
ማችን አልፈን እጅግ አንመካም። ፲፬ወደ እናንተ
እንደማንደርስ አድርገን፥ ራሳችንን የምናመስ
ግን አይደለምና፤ ነገር ግን የክርስቶስን ሕግ
በማስተማር ወደ እናንተ ደርሰናል። ፲፭እኛስ በማ
ይገባ ሌላ በደከመበት እንመካም፤ ነገር ግን ሃይ
ማኖታችሁ እንድትሰፋ፥ የተሠራችላችሁ ሕግም
በእናንተ እንድትጸና ተስፋ እናደርጋለን። ፲፮አብ
ዝተንም እናስተምራችኋለን፤ ያንጊዜም መጠና
ችን ከሥራችን ጋር ከፍ ከፍ ይላል፤ እኛስ ቀና
ባልሆነውና በማይገባው አንመካም። ፲፯"የሚ
መካ ግን በእግዚአብሔር ይመካ።" ፲፰እግዚአ
ብሔር ያከበረው ብቻ ይከብራል እንጂ ራሱን
የሚያከብር የተመረጠ አይደለም።

## ምዕራፍ ፲፩

### ለእግዚአብሔር ስለሚደረግ ቅንዐት

፩በስንፍናዬ እናገር ዘንድ ጥቂት ልትታገሡኝ
ይገባ ነበር፤ ቢሆንም በርግጥ ታገሡኝ፤ ፪ለእ
ግዚአብሔር የሚገባ ቅንዐት እቀናላችኋለሁና፤
ወደ እርሱ አቀርባችሁ ዘንድ ለአንዱ ንጹሕ
ድንግል ሙሽራ ለክርስቶስ አጭቻችኋለሁና።፩
፫ነገር ግን አባብ ሔዋንን በተንኰሉ እንዳሳ
ታት፥ አሳባችሁ ከክርስቶስ የዋህነትና ንጽሕና
ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ። ፬ወደ
እናንተ የመጣና እኛ ወደ አላስተማርናችሁ ወደ
ሌላ ኢየሱስ የጠራችሁ ቢኖር፥ ወይም ያልተቀ
በላችሁት ሌላ መንፈስ ቢኖር፥ ወይም ያልተማ
ራችሁት ሌላ ወንጌል ቢኖር ልትጠብቁን ይገ
ባል። ፭እኔ ግን ሌሎች ሐዋርያት ከአስተማሩት
ያጕደልሁባችሁ የለም ይመስለኛል።፪

### ወንጌልን ያለ ዋጋ ስለ ማስተማር

፮እኔ በአነጋገሬ አላዋቂ ብሆንም በዕውቀት ግን
እንዲሁ አይደለሁም፤ ነገር ግን ሁሉን በሁሉ አገ
ልጥላችኋለሁ። ፯ወይስ ራሴን በሁሉ ያዋረድሁ
በደልሁ ይሆን? እናንተ ከፍ ከፍ ትሉ ዘንድ፥
የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ዋጋ አስተምሬአች
ኋለሁና። ፰እናንተን አገለግል ዘንድ፥ ከሌሎች
አብያተ ክርስቲያናት ተቀብዬ፥ ለምግቤ ያህል
ወሰድሁ፤ ፱ከእናንተ ዘንድ በነበርሁበት ጊዜም፥
ስቸገር ገንዘባችሁን አልተመኘሁም።፫ ባልበቃ
ኝም ጊዜ ወንድሞቻችን ከመቄዶንያ መጥተው
አሟሉልኝ፤ በእናንተም ላይ እንዳልከብድባ
ችሁ በሁሉ ተጠነቀቅሁ፤ ወደ ፊትም እጠነቀ
ቃለሁ። ፲የክርስቶስ ዕውነት እብሮኝ ይኖራልና፥
ይህቺ ደስታዬ፬ በአካይያ አውራጃ አልተከለከለች
ብኝም። ፲፩ስለምን ነው? አልወዳችሁምና ነውን?
እንደምወድዳችሁስ እግዚአብሔር ያውቃል።

---

፪ ግእዙ "... ያፈርሳል ..." ይላል።

፩ ግሪኩ "እናንተን ለአንድ ሙሽራ ለክርስቶስ ንጽሕት ድንግል አድርጌ አጭቻችኋለሁና" ይላል።

፪ ግሪኩ "ከእነዚህ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በአንድ ነገር እንኳ እንደማንስ ራሴን አልቈጥርም" ይላል።

፫ ግሪኩ "በማንም አልከበድሁም" ይላል።

፬ ግሪኩ "ትምክሕቴ" ይላል።

፲፥፲፯ ኤር. ፱፥፳፬። ፲፩፥፫ ዘፍ. ፫፥፩-፯፤ ፲፫። ፲፩፥፱ ፊል. ፬፥፲፭-፲፰።

፲፪ነገር ግን ያደረግሁትም ቢሆን፥ የማደር
ገውም ቢሆን፥ እነርሱ እንደ እኛ የሚመኩበ
ትን ያገኙ ዘንድ፥ ምክንያት የሚሹትን ምክ
ንያት እሳጣቸው ዘንድ ነው። ፲፫የሚተነኰሉ፥
ራሳቸውን የክርስቶስን ሐዋርያት የሚያስመ
ስሉ፥ ዐመፅንም የሚያደርጉ ሐሰተኞች ሐዋ
ርያት እሉና። ፲፬ይህም አያስደንቅም፤ ሰይጣን
ራሱ ተለውጦ እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላ
ልና። ፲፭መልአክተኞቹም የጽድቅ መላእክትን
ቢመስሉ፥ ይህ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜ
ያቸው ግን እንደ ሥራቸው ነው።

## ስለ መንፈሳዊ ትምክሕት

፲፮ደግሞም እንዲህ እላለሁ፦ ሰነፍ የሚ
ያደርገኝ አይኑር፤ ያም ባይሆን እኔ ጥቂት
እመካ ዘንድ እንደ ሰነፍ እንኳ ብሆን ተቀበ
ሉኝ። ፲፯ይህም ቢሆን የምናገረው ለእግዚአብ
ሔር የሚገባ አይደለም፤ ነገር ግን ስለዚህች
ትምክሕቴ እንደ ሰነፍ እናገራለሁ። ፲፰በሥጋዊ
ሥርዐት የሚመኩ ብዙዎች ናቸውና እኔ ደግሞ
እመካለሁ። ፲፱እናንተ ልባሞች ስትሆኑ ሰነፎ
ችን መስማት ደስ ያሰኛችኋልና። ፳የሚገዙአች
ሁንና የሚቀሙአችሁን፥ መባያ የሚያደርጓች
ሁንና የሚታበዩባችሁን፥ ፊታችሁንም በጥፊ
የሚመቱአችሁን ትታገሡአቸዋላችሁና። ፳፩እኛ
እንደ ደካሞች መሰለን እንደ ነበርን፥ ይህን
በውርደት እናገራለሁ፤ ነገር ግን ማንም በሚ
ደፍርበት እኔ ደግሞ እደፍራለሁ።

፳፪እነርሱ ዕብራውያን ቢሆኑ እኔም እንደ እነ
ርሱ ነኝ፤ እነርሱ እስራኤላውያን ቢሆኑ እኔም
እንደ እነርሱ ነኝ፤ እነርሱ የአብርሃም ልጆች
ቢሆኑ እኔም እንደ እነርሱ ነኝ። ፳፫እነርሱ የክ
ርስቶስ አገልጋዮች ቢሆኑም እኔም እንደ ሰነፍ
ለራሴ እናገራለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ እጅ
ግም ደከምሁ፤ ብዙ ጊዜ ተገረፍሁ፤ ብዙ
ጊዜም ታሰርሁ፤ ብዙ ጊዜም ለሞት ተዘጋ
ጀሁ። ፳፬አይሁድ አንዲት ስትቀር አምስት ጊዜ
አርባ አርባ ገረፉኝ። ፳፭ሦስት ጊዜ በበትር ደበ
ደቡኝ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ መቱኝ፤ መርከቤ
ሦስት ጊዜ ተሰበረች፤ በጥልቁ ባሕር ውስጥ
ሰዋኝ አድሬ፥ ሰዋኝ ዋልሁ። ፳፮በመንገድ ዘወ
ትር መከራ እቀበል ነበር፤ በወንዝም መከራ
ተቀበልሁ፤ ወንበዴዎችም አሠቃዩኝ፤ ዘመዶ
ቼም አስጨነቁኝ፤ አሕዛብ መከራ አጸኑብኝ፤
በከተማ መከራ ተቀበልሁ፤ በበረሃም መከራ
ተቀበልሁ፤ በባሕርም መከራ ተቀበልሁ፤ ሐሰ
ተኞች መምህራን መከራ አጸኑብኝ። ፳፯በድካ
ምና በጥረት፥ ብዙ ጊዜም ዕንቅልፍ በማጣት፥
በመራብና በመጠማት፥ አብዝቶም በመጾም፥
በብርድና በመራቆት ተቸገርሁ። ፳፰የቀረውንም
ነገር ሳልቈጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአ
ብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው። ፳፱ታሞ
እኔ የማላዝንለት ማን ነው? በድሎስ እኔ የማ
ልደነግጥለት ማን ነው?

፴መመካት የሚገባ ከሆነስ እኔም በመከራዬ
እመካለሁ። ፴፩ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ የሆነ
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብ
ሔር ሐሰት እንደማልናገር ያውቃል። ፴፪በደማ
ስቆ ከተማ ከንጉሥ አርስጣስዮስ በታች የሆነ
የአሕዛብ አለቃ ሊይዘኝ ወድዶ የደማስቆን
ከተማ ያስጠብቅ ነበር። ፴፫በቅርጫትም አድር
ገው በመስኮቱ በኩል በአጥሩ ላይ አወረዱኝ፤
ከእጁም አመለጥሁ።

## ምዕራፍ ፲፪

## ጳውሎስ ስላየው ራእይ

፩እነሆ መመካት ይቻለኛል፤ ነገር ግን አይጠ
ቅምም፤ ደግሞም ወደ ጌታ ራእይና መገለጥ
እሄዳለሁ። ፪በክርስቶስ ያመነ አንድ ሰው አው
ቃለሁ፤ ዘመኑ ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት
ነው፤ ነገር ግን በሥጋው ይሁን በነፍሱ እንጃ፥
እግዚአብሔር ያውቃል፤ ያን ሰው እስከ ሦስ
ተኛው ሰማይ ድረስ ነጥቀው ወሰዱት። ፫ያን
ሰው አውቀዋለሁ፤ በሥጋው ይሁን በነፍሱ
እንጃ እግዚአብሔር ያውቃል። ፬ወደ ገነትም
ነጥቀው ወሰዱት፤ በዚያም ሰው ሊናገረው የማ
ይችለውን የማይተረጐም ነገር ሰማ። ፭ስለዚ
ህም እንደዚህ ባለው እመካለሁ፤ በመከራዬ
እንጂ በራሴስ አልመካም። ፮ልመካ ብሻም አላ
ዋቂ አይደለሁም፤ እውነቱን እናገራለሁና፤
ነገር ግን ስላዩኝና ስለ ሰሙኝ እንደምበልጥ
አድርገው እንዳይጠራጠሩኝ ትቻዋለሁ። ፯ስለ
ዚህም ቢሆን በብዙ ራእይ እንዳልታበይ ለሥ
ነቴን የሚወጋ እርሱም የሚጐስመኝ የሰይጣን
መልአክተኛ ተሰጠኝ። ፰ስለዚህም ከእኔ ያር
ቀው ዘንድ ጌታዬን ሦስት ጊዜ ማለድሁት።
፱እርሱም፥ “ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኀይልስ በደዌ

---

፲፩፥፳፫ ሐ.ሥ. ፲፮፥፳፫። ፲፩፥፳፬። ዘዳ. ፳፭፥፫። ፲፩፥፳፭ ሐ.ሥ. ፲፮፥፳፪፤ ፲፬፥፲፱።
፲፩፥፳፮ ሐ.ሥ. ፱፥፳፫፤ ፲፬፥፭። ፲፩፥፴፪-፴፫። ሐ.ሥ. ፱፥፳፫-፳፭። ፲፪፥፬ ሉቃ. ፳፫፥፵፫።

ያልቃል” አለኝ፤ የክርስቶስም ኃይል በእኔ ላይ ያድር ዘንድ በመከራዬ ልመካ ወደድሁ። ፲ስለዚህም ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበልን፥ መሰደብን፥ መጨነቅን፥ መሰደድን፥ መቸገርንም ወደድሁ፤ መከራ በተቀበልሁ ጊዜ ወዲያውኑ እበረታለሁና።

### በቆሮንቶስ ሰዎች ላይ ስለ አደረገው ወቀሳ

፲፩እነሆ እናንተ ስላገበራችሁኝ በመመካቴ ሰነፍ ሆንሁ፤ ለእኔማ በእናንተ ዘንድ ልከብርና እናንተም ምስክሮች ልትሆኑኝ[፩] ይገባኝ ነበር፤ እኔ እንደ ኢምንት ብሆንም ዋናዎቹ ሐዋርያት ሁሉ ከሠሩት ሥራ ያጐደልሁባችሁ[፪] የለምና። ፲፪የሐዋርያት ምልክትስ በፍጹም ትዕግሥትና በተአምራት፥ ድንቅ ሥራ በመሥራትና በኃይላት ተደርጎላችኋል። ፲፫እከብድባችሁ ዘንድ ወደ እናንተ ካለመምጣቴ በቀር፥ ከአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያሳነስኋችሁ በምንድን ነው? ይህቺን በደሌን ይቅር በሉኝ።

፲፬እነሆ ወደ እናንተ ልመጣ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ ነገር ግን እልተፋጠንሁም[፫] ገንዘባችሁን ያይደለ፥ እናንተን እሻለሁና፤ ልጆች ለወላጆቻቸው ያይደለ ወላጆች ለልጆቻቸው ሊያከማቹ ይገባልና፤ ፲፭እኔ ግን እጥፍ ድርብ አወጣለሁ፤ ስለ ሕይወታችሁም ሰውነቴን አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እናንተንም እጅግ ብወዳችሁ ራሴን ወደድሁ። ፲፮እኔ አልከበድሁባችሁም፤ ነገር ግን ምክር ዐዋቂ ሆኜ በመጠበብ ወሰድኋችሁ። ፲፯በውኑ ይህን አድርጉልኝ ብዬ ወደ እናንተ የላክሁት መልእክት አለን? ወይስ የቀማኋችሁ ነገር አለን? እንጃ። ፲፰እነሆ ቲቶን ማለድሁት፤ ከእርሱም ጋር ሌላውን ወንድማችንን ላክሁት፤ በውኑ ቲቶ የበደላችሁ በደል አለን? በእርሱ በአደረው መንፈስ የምንመላለስ፥ እርሱም የሄደበትን ፍለጋ የምንከተል አይደለንምን?

፲፱እኛስ ደግሞ ስለ ራሳችን የምንከራከራችሁ ይመስላችኋልን? በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን፤ ወንድሞቻችን ሆይ፥ ይህ ሁሉ ግን እናንተ ትታነጹ ዘንድ ነው። ፳ነገር ግን ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ እንደምወደው ሆናችሁ ያላገኘኋችሁ እንደ ሆነ፥ እኔም እንደማትወዱት እሆንባችኋለሁ ብዬ እፈራለሁ፤ ወይም እኮ በመካከላችሁ ክርክር፥ ኵራት፥ መቀናናት፣ መበሳጨት፥ መዘባበት፥ ወይም መተማማት፥ መታወክ፥ ወይም ልብን ማስታበይ ይኖር ይሆናል። ፳፩ወይም እንደ ገና ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በእናንተ ምክንያት እግዚአብሔር ያሳዝነኝ ይሆናል፤ በድለው ንስሓ ሳልገቡም ስለ ርኩስነታቸውና ስለ መዳራታቸው፥ ስለሚሠሩት ዝሙታቸውም ለብዙዎች እዝን ይሆናል።

## ምዕራፍ ፲፫

### ቅዱስ ጳውሎስ ሦስተኛ ጊዜ ወደ ቆሮንቶስ ስለ መምጣቱ

፩ወደ እናንተ ስመጣ እነሆ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ ነገር ሁሉ፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ የሚጸና አይደለምን? ፪ጥንቱን አስቀድሜ ተናግሬእለሁ፤ አሁንም አስቀድሜ እናገራለሁ፤ ቀድሞ ከእናንተ ጋር ሳለሁ እንደ ነገርሁእችሁ፥ አስቀድሞ ለበደሉ፥ ለሌሎችም ሁሉ እንደ ገና የመጣሁ እንደ ሆነ ርኅራኄ እንዳላደርግ፥ እንዲሁ ሳልኖር ለሦስተኛ ጊዜ እናገራለሁ፥ ፫ክርስቶስ በእኔ አድሮ እንደሚናገር ማስረጃ ትሻላችሁና፤ እርሱም ሁሉ የሚቻለው ነው እንጂ፥ በእናንተ ዘንድ የሚሳነው የለም። ፬በድካም ተሰቅሎእልና፤ በእግዚአብሔርም ኃይል ሕያው ነውና፤ እኛም ከእርሱ ጋር እንደከማለንና፤ ነገር ግን ስለ እናንተ በሚሆን በእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ ጋር በሕይወት እንኖራለን።

፭በሃይማኖት ጸንታችሁ እንደ ሆነ ራሳችሁን መርምሩ፤ እናንተ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናንተ ጋር እንዳለ አታውቁምን? እንዲህ ካልሆነ ግን እናንተ የተናቃችሁ ናችሁ። ፮እኛም ብንሆን የተናቅን እንዳይደለን እንደምታውቁ እኔ አምናለሁ። ፯ምንንም ክፉ ሥራ እንዳትሠሩ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፤ መልካም ነገር እንድታደርጉ ብቻ ነው እንጂ እኛ ደጎች ልንባል አይደለም፤ እኛም እንደ ተናቁ ሰዎች እንሆናለን። ፰ለእውነት ጸንተን እንኖራ

---

፩ “እናንተም ምስክሮች ልትሆኑኝ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ “ከዋናዎቹ ሐዋርያት በምንም አልጐድልም” ይላል።

፫ ግሪኩ “እልከበድሁባችሁም” ይላል።

፲፪፥፲ ማቴ. ፭፥፲፩-፲፪። ፲፪፥፲፪ ሮም. ፲፭፥፲፱። ፲፪፥፲፭ ፊል. ፪፥፲፯። ፲፪፥፳ ፩ቆሮ. ፩፥፲፩።
፲፪፥፳፩ ፩ቆሮ. ፭፥፩። ፲፫፥፩ ዘዳ. ፲፯፥፮፤ ፲፱፥፲፭። ፲፫፥፫ ፩ ቆር. ፭፥፬። ፲፫፥፬ ፊል. ፪፥፯፡፰።

ለን እንጂ፤ ከእውነት መውጣት አንችልምና። ፱እና
ንተ ትበረቱ ዘንድ እኛ ስንደክም ደስ ይለናል። ጸሎ
ታችንም እናንተ ፍጹማን ትሆኑ ዘንድ ነው።

### ሰላምታና ቡራኬ

፲ስለዚህም እግዚአብሔር ለማፍረስ ያይደለ ለማ
ነጽ በሰጠን ሥልጣን ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ
ቍርጥ ነገር እንዳላደርግባችሁ፥ ሥልጣን እንዳለው
ሰው ከእናንተ ጋር ሳልኖር ይህን እጽፋለሁ።
፲፩ወድሞቻችን ሆይ፥ እንግዲህ ደስ ይበላችሁ፤
ጽኑ፤ ታገሡ፤ በአንድ ልብም ሁኑ፤ በሰላም ኑሩ፤
የሰላምና የፍቅር አምላክም ከእናንተ ጋር ይሁን።
፲፪በተቀደሰ ሰላምታ እርስ በርሳችሁ ሰላም ተባባሉ፤
ቅዱሳን ሁሉ እንዴት ናችሁ? ይሏችኋል። ፲፫የጌ
ታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር
ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችሁ ጋር
ይሁን። አሜን።

የመቄዶንያ ክፍል በምትሆን በፊልጵስዩስ ተጽፎ በቲቶና በሉቃስ እጅ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው ሁለተኛዉ መልእክት ተፈጸመ።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፤ አሜን።

---

፲፫፥፲፩ ሮም. ፲፭፥፴፫። ፲፫፥፲፪ ፩ቆሮ. ፲፮፥፳።